# የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የህግ ማንዋል

ACLP

CIVIL SOCIETY
RESOURCE CENTER

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ

Ferderal Democratic Republic of Ethiopia
AGENCY FOR CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS

# ማውጫ


**የዋና ዳይሬክተሩ መልእክት** 2
**ማስተባበያ** 3
**ምዕራፍ 1: መግቢያ** 6
አዲስ የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊነት 7
በአዲሱ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1113/2010 የተደረጉ አንኳር ለውጦች 10
**ምዕራፍ 2 : የተፈፃሚነት ወሠን** 16
**ምዕራፍ 3: የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ** 20
የኤጀንሲው አላማዎች 21
የኤጀንሲው ስልጣንና ሃላፊነት 21
የኤጀንሲው አደረጃጀት 23
ቦርዱ 23
ዳይሬክተሩና ምክትል ዋና ዳይሬክተር 24
**ምዕራፍ 4 : ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምስረታ እና ምዝገ ባ መርሆዎች** 26
የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚቋቋሙበት መርሆዎች 27
የምዝገባ ሂደት 28
**ምዕራፍ 5 : የበጎ አድራጎት ድርጅትና ማህበራት አይነቶች** 30
የውጭ እና ሀገር በቀል ድርጅቶች 31
የውጭ ድርጅቶች 31
የሀገር በቀል ድርጅቶች 32
**ምዕራፍ 6 : በአዲሱ አዋጅ የተካተቱ የሰራ ጉዳዮች** 36
የስራ ነፃነት 37
ሀብት፣ የማፈላለግ፣ የመቀበል እና የመጠቀም መብት 38
ውስጣዊ የፋይናንስ ቁጥጥር ስርዓት 39
የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አመራር 39
ሪፖርት እና ቁጥጥር 40
የሪፖርት አይነቶች እና የሚቀርብበት ጊዜ 40
ሪፖርት 41
እርምጃዎች 42
መዋሃድ፣ መከፈል እና መለወጥ 42
አስተዳደራዊ እርምጃዎች 43
ማስጠንቀቂያ 44
እገዳ 44
መፍረስ እና ከመዝገብ መሠረዝ 44
የመሰማት መብት 45
የመፍረስ ውጤቶች 45
ራስን የማስተዳደር ማዕቀፍ 46

# ኢፌድሪ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ

## የዋና ዳይሬክተሩ መልእክት

አገራችን ኢትዮጵያ ሀገር ዐቀፍ እና መጠነ ሰፊ የሆነ የለውጥ ሂደት የጀመረች ሲሆን ይህም ለውጥ በሕብረተሰቡ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ህይወት ላይ እንዲሁም በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ላይ አዎንታዊ የሆነ ለውጥን አምጥቷል። ለዚህም እንደ ማሳያ ሊጠቀስ የሚገባው መንግስት በለውጡ ማግስት ጊዜ ሳያጠፋ ኢትዮጵያባለፋት አመታት ካፀደቀቻቸው አሳሪ ህጎች መካከል አንዱ የሆነውን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ 621/2001 በመሻር አዲስ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ 1113/2011 ማውጣቱ ነው። አዲሱ ህግ ሲቀረፅም በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ሥር በተደራጀው የህግና ፍትህ ጉዳዮች አማካሪ ም/ቤት ሥር በተደራጀው ገለልተኛ የህግ ባለሙያዎች ቡድን አማካኝነት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን በሰፊው ያሳተፈና አዋጁ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጥር 28 ቀን 2011 ከመፅደቁ በፊት ጥልቅ ውይይት የተደረገበት ነበር።

የአዲሱ ሕግ ዓላማ በህገመንግስቱ እና በዓለም ዐቀፉ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች የተረጋገጠውን የመደራጀት መብትን ማክበር እና ማስከበር ሲሆን ይህም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በአገሪቱ ቀጣይነት ያለው ልማት፤ ዲሞክራሲና ሰላም መረጋገጥ የሚኖራቸውን ሚና ከፍ ማድረግ፤ እንዲሁም የህብረተሰቡን የላቀ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በተሻለ ሚናቸውን እንዲጫወቱ ማስቻል ነው። አዲሱ ሕግ ከፀደቀ በኋላ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲም ለውጡን ለማሳካት የተቻለውን ጥረት ሁሉ በማድረግ ላይ ሲሆን በዚሁ መሰረት ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ገንቢ እና መልካም የሆነ ግንኙነት በመፍጠር፤ እንዲሁም የተሻለና ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት ለአዲሱ ህግ ተፈፃሚነት የበኩሉን ሚና በማበርከት ላይ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ ኤጀንሲው የተለያዩ የአቅም ግንባታ፤ የአሰራር አማራጮች፤ የአዋጁን ማስፈጸሚያ ደንብና መመሪያዎችን ማዘጋጀት እንዲሁም የተለያዩ ሕብረተሰቡን የማንቃት ስራዎችን እየሰራ ይገኛል።

ከላይ የተመለከቱትን ለማሳካት ኤጀንሲው ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ጋር እየሰራ የሚገኝ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የአፍሪካ ሲቪክ ሊደርሺፕ ፕሮግራም (ACLP) አንዱ ሲሆን ኤጀንሲውም ከአፍሪካ ሲቪክ ሊደርሺፕ ፕሮግራም ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በሕግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በተሻለ መንገድ በመወጣት ላይ ይገኛል። ከዚህም በተጨማሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ እና የአፍሪካ ሲቪክ ሊደርሺፕ ፕሮግራም በጋራ በመሆን ሕብረተሰቡ፤ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና ማንኛውም ፍላጎቱ ያለው ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ማቋቋም ሲፈልግ ሊጠቀምበት የሚችል ይህንን የተገልጋዮች መጠቀሚያ ማኑዋል አዘጋጅተዋል።

ይህ ማንዋል ሲዘጋጅ በተቻለ መጠን የተለያየ እውቀትና ግንዛቤ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎችን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ቀላልና ለተጠቃሚው ምቹ ሆኖ የቀረበ ሲሆን፤ ማንዋሉ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ምቹ የእንቅስቃሴ ምህዳር ከመፍጠርና በሀገር ልማት፤ ዴሞክራሲያዊ እና ሰላም ግንባታ ላይ ያላቸውን ሚና ከማሳለጥ አኳያ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል የሚል እምነ ት አለኝ።

በዚህ አጋጣሚ ለአፍሪካ ሲቪክ ሊደርሺፕ ፕሮግራም (ACLP) ያለኝን ከፍ ያለ ምስጋና እንዲሁም ላደረጉልን የገንዘብ እንዲሁም የተለያዩ ድጋፎች ያለኝን አድናቆት ለመግለጽ እወዳለሁ።

ጂማ ዲልቦ  
ዋና ዳይሬክተር  
ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ

# ማስተባበያ

በዚህ ፅሁፍ ላይ የተካተቱት ሃሳቦች የፀሃፊው ናቸው፤ ሃሳቦቹም የ `ACLP` ን አቋም ላያንፀባርቁ ይችላሉ።

# ምህጻረ ቃላት

ACLP – የአፍሪካ ሲቪክ ሊደርሺፕ ፕሮግራም

ACSO – የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ

CSO– ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች (ሲማድ)

CSP –የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ 621/2001

CSOP –የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ 1113/2011

LJAAC – የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ

# ምዕራፍ 1
# መግቢያ

# ምዕራፍ 1

# መግቢያ

## 1.1 አዲስ የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊነት

የመደራጀት መብት በኢትዮጵያ ህገ-መንግስትና ኢትዮጵያ ተቀብላ ባፀደቀቻቸው ዓለም ዓቀፍ የሰብአዊ መብት ቃልኪዳን ሰነዶች ውስጥ ከሚገኙ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች ውስጥ አንዱ ነው። የኢፌዴሪ ህገ-መንግስትም አንቀጽ 31 ዜጎች ለማንኛውም ህጋዊ ዓላማ መደራጀት እንደሚችሉ ይገልጻል። ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው ዓለም ዓቀፍዊ እና ቀጠናዊ ቃልኪዳኖችም ይህንኑ ይገልጻሉ። የሲቪል ማህረሰብ ድርጅቶችም የመደራጀት መብት ዋነኛው መገለጫዎች ናቸው። ከመደራጀት መብት መከበር ባለፈም የሌሎች መሠረታዊ መብቶች መከበር እና መጎልበት ጉልህ ሚና ይጫወታሉ። ስለዚህም ይህንን ዘርፍ ለመቆጣጠር የሚወጡ ማናቸውም የህግ ማዕቀፎች የሲቪል ማህበረሰብ አደረጃጀቶች ለማቋቋም እና ዓላማቸውንም ለማስፈጸም ምቹ ከባቢን መፍጠር ይኖርበታል። ይህም በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ቀጣይነት ያለውን ልማት እና ዴሞክራሲ ከሚያመጡ ተቋማት ግንባር ቀደም እንዲሆኑ ያስችላቸዋል።

ከዚህም ጋር ተያይዞ ዓለም ዓቀፍ መመዘኛዎች እና ውጤታማ የሆኑ ተሞክሮዎች የሚያሳዩት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የሚመለከቱ ህጎች ከማፈን፣ከመከላከልና ከመቅጣት ይልቅ ምቹ ሁኔታን የመፍጠር እና ድጋፍ መስጠት ላይ ማተኮር እንዳለባቸው ነው። የምዝገባ ስርዓቱም ፈጣን፣ግልጽ እና ቀላል መሆን እንዳለበት ያስቀምጣሉ። የተቆጣጣሪ ኤጀንሲውም ተግባር የድርጀቶች እራስን በራስ የማስተዳደር መብት በማክበር ከህጉ ጋር አብረው መሄዳቸውን ማረጋገጥ እና አቅማቸውን መገንባት መሆን ይገባዋል። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችም ቢሆኑ የተቆጣጣሪውን አካል ውሳኔዎች ለፍ/ቤት ይግባኝ የማለት የሁልጊዜ መብት ሊኖራቸው ይገባል። ከፈለጉት ህጋዊ የገቢ ምንጭ ገንዘብ የማግኘት እና የመጠቀም መብት ሲኖራቸው አባላቱ አሊያም መስራቾቹ የድርጅቱን ሕጋዊ ዓላማ የመወሰን ነጻነት ሊኖራቸው የግድ ይላል።

ይህ ሆኖ ሳለ ላለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ዘርፉን ሲቆጣጠር የነበረው አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከላይ ከተጠቀሱት ዓለም ዓቀፍ እና ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎች በአውድም ሆነ ከህጎቹ መንፈስ የራቀ ሆኖ እናገኘዋለን። በመጀመሪያ ደረጃ ህጉ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሚል ትክክለኛ ያልሆነ ክፍፍል ላይ ተመርኩዞ የወጣ ነው። ገዢው ፓርቲ በተለያዩ መንገዶች በተደጋጋሚ ሲገልጸው እንደነበረው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እንደ ብዙኃን ማህበራት ማለትም የሴቶች ማህበር፣ የወጣቶች ማህበር እና የመሳሰሉት ተደርገው ሲወሰዱ ሁሉም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሆነው ከውጭ ገቢ የሚያገኙት ደግሞ የውጭ አካላት አጀንዳ ተቀባይ እና በሀገር ውስጥም ምንም አይነት ቅቡልነት እንደሌላቸው፣ ስለሆነም ከሰብዓዊ መብት፣ከፆታ እኩልነት፣ መቻቻል እና አስተዳደር ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ምንም እንቅስቃሴ ማድረግ እና መሳተፍ እንደማይችሉ ይገለጽ ነበር። ይህ አመለካከት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት/ማህበር እና የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት/ማህበር ለሚል መከፋፈልና ለኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅትን/ማህበርን ደግሞ ከስራ እንቅስቃሴ አኳያ፣ በሪፖርት አቀራረብ ረገድ እና ለፍ/ቤት ይግባኝ ከማለት መብት አንጻር አድልዎ እንዲደርስበት አድርጓል።

በውጤቱም ህጉ ከሚከተሉት አንኳር ነጥቦች አንፃር ዓለም ዓቀፍ እና ህገ-መንግስታዊ መመዘኛዎችን አያሟሏም ነበር። በመጀመሪያ በአዋጁ አንቀጽ 14 ላይ ከተጠቀሱት ዓላማዎች ለማስፈጸም ካልሆነ በስተቀር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መቋቋም አይቻልም ሲል ዜጎች ለፈለጉት ዓላማ ድርጅቶችን እንዳያቋቁሙ ይገድባል። ይህም ህገ-መንግስታዊ የሆነውን ለማንኛውም ህጋዊ ዓላማ የመደራጀትን መብትን ይጻረራል።

ሁለተኛ አዋጁ በልማት እና አገልገሎት መስጠት ላይ የተሰማሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከውጭ ገቢ እንዲያገኙ ሲፈቅድ ነገር ግን በሰብዓዊ መብት፣ የፆታ እኩልነት፣ የአካል ጉዳተኞች መብት፣ የህፃናት መብት፣ የፍትሕ ዘርፍ እንዲሁም የሃይማነት እና የዘር መቻቻል እንዲጎለበት የሚሰሩ ድርጅቶች ከ90 ከመቶ ወይም ከዛ በላይ የሆነ ገቢያቸውን ከሃገር ውስጥ ምንጮች ማግኘት አለባቸው በማለት በድርጅቶች መካከል አድሎን ፈጥሮአል። አድልዎ ከማድረግ እና የመደራጀትን መብትን ከመገደብ ባለፈ ይህ አሰራር በሰብዓዊ መብት ዙሪያ የሚሰሩ ድርጅቶችን በማፈን የዜጎችን መብት በተለይም ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖችን መብት መጠበቅ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል።

በሦስተኝነት የቀድሞ አዋጅ መብት ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች መብት ላይ መስራታቸውን ትተው አገልግሎት መስጠት ላይ ብቻ እንዲሰማሩ አስገድዷል። ይህም የሲቪል ማህበረሰብ ደርጅቶች ዜጎችን ስለመብታቸው በማስተማር፤ ዜጎች እንዲበቁ የሚደርጉትን ጥረት አደናቅፏል። ከሃገር ውስጥ ገቢን ማሰባሰብ ብዙ ተግዳሮቶች አሉት። ከእነዚህም መካከል የሚጠቀሱት ድህነት፣ መሰል ዓላማዎችን በገንዘብ የመደገፍ ባህል አለመኖር እንዲሁም ከመንግስት ሊመጣ የሚችለውን ተፅዕኖ መፍራት ይጠቀሰሳሉ። በዚህም ምክንያት በሃገር ውስጥ የነበሩት ጥቂት የመብት ድርጅቶች ዓላማቸውን ቀይረዋል አሊያም በተገደበ መልኩ ለመንቀሳቀስ ተገደዋል።

በአራተኛ ደረጃ አዋጁ ኤጀንሲው ከመመዝገብ፣ ከማገድ እና ከማፍረስ ጋር ተያይዞ ለሚሰጣቸው ውሳኔዎች ለፍ/ቤት ይግባኝ የማለትን መብት ለኢትዮጵያ የበጎ አድራገት ድርጅቶች ብቻ በመስጠት አሁንም አድልዎ ያደርጋል። ይህም ማለት ዜጎች የመደራጀት መብታቸው ቢጣስ እንኳን የገቢ ምንጫቸው ከውጭ ስለሆነ ብቻ ይግባኝ የማለት መብታቸው ይነፍጋል።

አምስተኛ በኤጀንሲው የሚወጡ መመሪያዎች በጎ አድራጎተችን ከሌሎች ተመሳሳይ ማህበራት ጋር ህብረት መፍጠርን ይከለክላል። የውጭ እና የነዋሪዎች ማህበራትም ከኢትዮጵያ ማህበራት ጋር ህብረት መፍጠር አይችሉም ነበር። የሲቪል ማህበራትም ኔትዎርክ ቢፈጥሩ የሚያርጉት መዋጮ እንደአስተዳደራዊ ወጪዎች ስለሚቆጠሩ ኔተዎርክ ከመፍጠር ይታቀቡ ነበር።

ሰድስተኛ የ70/30 መመሪያ ነው። ይህም አብዛኛውን የፕሮግራም ወጪዎች እንደ አስተዳደራዊ ወጪ የሚቆጥር ነው። የአስተዳደራዊ ወጪዎች ደግሞ ከድርጅት በጀት 30 ከመቶ በላይ መሆን አይችሉም። ይህም ገደብ ድርጅቶች በቂ ሰራተኞች እንዳይቀጥሩ፣ በገጠር አካባቢ ተዘዋውረው እንዳይሰሩ፣ ጥናት እና ምርምር እንዲሁም ስልጠናዎችን እንዳያካሂዱ እነዚህ ወጪዎች እንደ አስተደዳደራዊ ወጪዎች ተቆጥረው ቆይተዋል። ይህም ድርጅቶችን ገደቦ ለመንቀሳቀስ ከባድ አለፍ ሲልም የማይቻል ሆኖባቸው ቆየቶዋል።

በሰባተኛ ደረጃ አዋጁ ድርጅቶች ከስራቸው ጋር በተያያዘ እንቅስቃሴዎች ላይ ብቻ በመሳተፍ ገቢ ማግኘት እንደሚችሉ ይደነግጋለል። ይህም የመብት ድርጅቶች እንቅስቃሴ ለንግድ ምቹ ስላልሆነ ገቢ ለማግኘት ማነቆ ሆኖባቸው ቆይቶዋል።

በመጨረሻም አዋጁ ለበጎ አድራገት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን እንዲያግድ፣ እንዲያፈርስ እና ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎችን እንዲወስድ ሰፊ ስልጣን ሲሰጠው በምላሹ ግን ኤጀንሲው ለሚያደርሳቸው ጥሰቶች እና ጉዳቶች ምንም አይነት ጥበቃ አያደርግም።

በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ህጉ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ አፋኝነቱ ስለሚታወቅ የኢትዮጵያን ገፅታ የሚያጎድፍ ሆኖ ቆይቶዋል።


በመጋቢት 2010 በኢትዮጵያ አዲስ የለውጥ አመራር ወደ ስልጣን መምጣቱን  ተከትሎ መንግስት አፋኝ ህጎችን ለመቀየር ያለውን ቁርጠኝነት  ገለፀ። ለዚህም የሕግ እና የፍትሕ ማሻሻያ ጉባኤ አቋቁሞ ወደ ስራ ገባ። በዚህ ጉባኤ ከተቋቋሙት የስራ ቡድኖች መካከል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ህግ የሚያሻሽለው አንዱ ሲሆን በአዋጁ ላይም ጥልቅ የሆነ ጥናት አካሄዷል። በጥናቱ ለላይ ተመርኩዞ ጉባኤው የቀድሞው አዋጅ የመደራጀት መብትን በጠበቀ እና በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ላይ ያሉ ገደቦችን በሚያነሳ አዲስ አዋጅ መተካት እንዳለበት ምክረ ሀሳብ አቀረበ። በዚህም መሰረት አዲስ የተረቀቀው አዋጅ ዓለም ዓቀፍ ቃልኪዳኖችን ባከበረ እና መልካም ተሞክሮዎችን በመውሰድ ነበር። የተካሄዱት ምርምሮች እና ግኝቶችም ከባለድርሻ አካላት ማለትም ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ከኤጀንሲው፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም ሚድያዎች ጋር ውይይት ተድርጎባቸዋል።  የምክክር ፎረሞቹም በዘጠኙም  ክልሎች አዲስ አበባ እና ድሬዳዋን ጨምሮ  ከኢትዮጵያ በጎ አድራጎት እና ማህበራት ፎረም ጋር በመተባበር ተዘጋጅቷል። ከውጭ ድርጅቶች እና በአካል ጉዳተኝነት ላይ ከሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ  ድርጅቶችም ጋር በልዩ ሁኔታ ውይይቶች ተደርጎዋል። በምክክሮችም መሠረት ማሻሻያዎች ተደርገው ረቂቁ በሚኒስትሮች ም/ቤት ተቀባይነትን ካገኘ በኋላ ጥቂት ለውጦች ተደርጎበት በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሊፀድቅ ችሎዋል።

## 1.2 በአዲሱ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1113/2010 የተደረጉ አንኳር ለውጦች

ከላይ እንደተገለፀው አዲሱ የሲቪል ማህበረሰብ አዋጅ የቀድሞውን የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጅ ህገ-መንግስታዊ የሆነውን የመደራጀት መብት ከማክበር አንፃር ያሉ ክፍተቶችና ግድፈቶችን በጥልቅ በመመርመር የተገኘ አዋጅ ነው። በዓለም ዓቀፍ መመዘኛዎችና ተሞክሮዎች እንዲሁም ከተደረገው ጥልቅ ጥናት ተመርኩዞ አዲሱ የሲቪል ድርጅቶች አዋጅ በኢትዮጵያ ላሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አቅም የማጎልበቻ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ታቅዶ የተዘጋጀ ነው። አዋጁም የዜጎችን ለማንኛውም ህጋዊ ዓላማ የመደራጀትን መብት ያረጋገጠ ነው። ለዚህም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከገቢ ምንጫቸው አንፃር ያለውን ክፍፍል አስቀርቶታል። ከዛም ባለፈ ከማንኛውም ህጋዊ ምንጭ ገቢ የማግኘት እንዲሁም በፈለጉት የንግድ ስራ ተሰማርተው ገቢ የማግኘት መብት ያጎናፅፋቸዋል። አስተዳደራዊ ወጪዎችንም ከፕሮግራም ጋር የተያያዙ ወጪዎችን በማስወጣት አስተዳደራዊ ጉዳዮች ጋር ብቻ የተያያዙ በማለት ይተረጉመዋል። በኤጀንሲውም ሰፊ የሆነ የቦርድ ውክልና ለድርጅቶች ይሰጣል። ከምዝገባ ጋርም በተያያዘ ቀላልና ፈጣን የሆነ የምዝገባ ስርዓት አቅርቧል። የኤጀንሲውንም ማንኛውም አይነት ውሳኔዎች በፍ/ቤት ይግባኝ የማለት መብት ያጎናፅፋል። የኤጀንሲውንም ዋነኛ ዓላማ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የመደገፍና አቅም የመገንባት እንደሆነ በመግለፅ የቅጣት እርምጃዎች እንደመጨረሻ አማራጭ ሆነው ሊተገበሩ የሚችሉትም ለድርጅቶች ስህተታቸውን እንዲያርሙ ዕድሉን በመስጠትና በአግባቡ ምክንያታቸውን በመስማት ነው። በኤጀንሲው የተወሰዱ እርምጃዎችም በቦርዱ አሊያም በፍ/ቤት ሊታዩ ይችላሉ።

አዲሱ አዋጅ ህብረት እንዳይፈጠር የሚደረገውን ገድብም በማንሳት የህብረቶችም ህብረት መፍጠር የሚያስችል ሁኔታን ያመቻቻል። አዋጁን ለማስፈፀም ዋነኛ ተዋንያን ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶቹ ራሳቸው ናቸው በሚል ዕምነት አዲሱ አዋጅ የራስን አስተዳደር ሀሳብ አስተዋውቋል። ለዚህም የድርጅቶችን ም/ቤት አቋቁሟል። ም/ቤቱም የሥነ-ምግባር መተዳደሪያ ደንብን ያወጣል፤ ተፈፃሚነቱንም ይከታተላል።

የሚከተለው ሠንጠረዥም አዋጁ ያስተዋወቃቸውን ለውጦች ጠቅለል ባለ መልኩ ያስቀምጣል።



| ክፍል | የቀድሞ አዋጅ | አዲሱ አዋጅ |
|---|---|---|
| መግቢያ | የዜጎች የመደራጀት መብትን አያረጋግጥም። <br>የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ለልማት ያላቸውን ፋይዳ ያሳልጣል። | • የመደራጀት መብት መከበር ለሌሎች መብቶች መከበር ያለውን ሚና ይገነዘባል። <br>• የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መንግስትን ግልፅ፣ ተጠያቂ እና አሳታፊ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ያላቸውን ሚና ይገነዘባል። <br>• ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምቹ የሆነ ሁኔታ መኖር ድርጅቶች ለልማት እና ዴሞክራሲ ለሚያደርጉት ድጋፍ አስፈላጊ እንደሆነ ይገነዘባል። <br>• በዘርፉ ያለውን ነፃነት እና ተጠያቂነት ሚዛናዊ መሆን እንዳለበት ይገነዘባል። <br>• በሕብረተሰቡ ዘንድ በጎ አድራጎት በጎ ፈቃደኝነት ባህል መዳበር አስፈላጊ መሆኑን ይገነዘባል። <br>• በቀድሞ አዋጅ የነበሩትን ክፍተቶች መሙላት |
| የተፈፃሚነት ወሰን | • ከአንድ ክልል በላይ እና አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶቸ <br>• የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶች <br>• በአንድ ክልል ብቻ የሚሰሩ ሆነው ገቢያቸው ከውጭ የሆኑ ድርጅት | • በሁለት እና ከዚያ በላይ ክልሎች እና በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ የሚንቀሳቀሱ ሀገር በቀል እና የውጭ ድርጅቶች <br>• በአንድ ክልል ብቻ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች የትኛውም አይነት የገቢ ምንጭ ቢኖራቸውም አዋጁ ተፈፃሚ አይደረግባቸውም። |
| የኤጀንሲው የቦርድ አወቃቀር | • ድርጅቶች በቂ ውክልና አልነበራቸውም <br>• ከ7 የቦርድ አባላት 2 ብቻ ከድርጅቶች ይመረጣሉ | • ተመጣጣኝ እና አሳታፊ የሆነ የድርጅቶች ውክልና <br>• 3 ከመንግስት አካላት፣ 3 ከሲቪል ድርጅቶች፣ 2 ከአካል ጉዳተኞች ፌደሬሽን፣ 2 ከወጣት እና ሴቶች ማህበራት እና 1 ገለልተኛ ባለሞያ |

| | | |
|---|---|---|
| የተቆጣጣሪ ኤጀንሲው ኤጀንሲ ሥልጣን | • በመቆጣጠር እና ቅጣት ላይ ያተኩራል<br>• በጣም ሰፊ የሆነ የመወሰን ሰልጣን ለኤጀንሲው ይሰጣል።<br>• አብዛኛው ውሳኔዎች በፍ/ቤት የመታየት ዕድል የላቸውም<br>• ሰፊ እና ጠቅለል ያለ በመሆኑ የተነሳ ኤጀንሲውም ለመተግበር ከባድ ሆኖበት  ቆይቷል። | • የድርጅቶችን እንቀስቃሴ ይደግፋል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤<br>• የራሳቸው የሆነ የውስጥ አስተዳደር እንዲኖራቸው ይደግፋል።<br>• በጎ አድራጎትንና በጎ ፈቃደኝነትን ያበረታታል<br>• የድርጅቶች ድጋፍ ፈንድ ያቋቁማል<br>• አጣሪዋችን በማዘጋጀት ስራቸውን ይከታተላል<br>• የድርጅቶች እንቅስቃሴዎች ከመንግስት ዕቅዶች ጋር በተቻለ መጠን ተመጋጋቢ መሆናቸውን ለማረጋገጥ መመሪያ ያዘጋጃል<br>• ጥናት እና ምርምር በማካሄድ ድርጅቶቹ ለልማት፣ ሰብዓዊ መብት መከበርእና ዴሞክራሲን ለማስፈን ያላቸውን ሚና ለመንግስት ያማክራል |
| የቦርዱ ሥልጣን | ጠቅለል ያለና ቦርዱም ኤጀንሲውን ተጠያቂ እንዲያደርረግ አቅም አይሰጠውም | • የመደራጀት መብት በሙሉ ሁኔታ እንዲከበር እና ድርጅቶች ከዘርፉ ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ አቅጣጫ ያስቀምጣል<br>• የኤጀንሲው ዳይሬክተርን ውሳኔዎች በይግባኝ መልክ የያል<br>• የኤጀንሲውን ዳይሬክተር እና ምክትል ዳይሬክተር ተግባር ይገመግማል<br>• ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው የሥነ-ስርዓት ደንብ ያወጣል፤ ተፈፃሚነቱንም ይከታተላል<br>• ድርጅቶች አዋጁ ላይ በተጠቀሰው መሠረት እንዲንቀሳቀሱ መመሪያ ያወጣል<br>• ከኤጀንሲው ዳይሬክተር የሚላኩ አመታዊ ዕቅዶችንና ሪፖርቶችን መርምሮ ያፀድቃል |
| የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አይነቶች | በአወቃቀር እና በገቢ ምንጭ ነው የተመደቡት<br>• የኢትዮጵያ በጎ  አድራጎት ድርጅት<br>• የኢትዮጵያ ማህበር<br>• የኢትዮጲያ ነዋሪዎች ማህበር<br>• የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅት<br>• የበጎ አድራጎት ተቋም<br>• የበጎ አድራጎት ማህበር | በገቢ ምንጭ ሳይሆን በአወቃቀር የተደረገ ክፍፍል<br>1. የውጭ ድርጅቶች<br>2. ሀገር በቀል ድርጅቶች<br>• ማህበራት<br>• ቦርድ መር ድርጅቶች<br>• የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት<br>• የአደራ  በጎ አድራጎት ድርጅት<br>• የበጎ አድራጎት ኮሚቴ |
| ህብረት ስለመፍጠር | • ማህበራት ከበጎ አድራጎቶች ጋር ህብረት መፍጠር አይችሉም<br>• የኢትዮጵያ በጎ አድራጎቶች ከነዋሪዎች እና የውጭ በጎ አድራጎቶች ጋር ህብረት መፍጠር አይችሉም<br>• ቀጥተኛ የሆነ የፕሮጀክቶች ትግበራ አይፈቀድም | • ህብረቶች ስለመፍጠር ምንም አይነት ገደብ የለም<br>• ተጨማሪ ስልጣኖች ለህብረቶች ይሰጣል<br>○ የአባላት የጋራ ድምፅ በመሆን የጋራ መብትን እና ጥቅምን ማስከበር<br>○ የአባላትን አቅም መገንባት እና ገንዘብ የማሰባሰብ ጥረታቸውን መደገፍ<br>○ አባላት በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የፖሊሲ ሙግት እና የድጋፍ ስራዎችን ማከናወን<br>○ ከአባላት ጋር ውድድር አለማድረግ<br>የህብረቶች ህብረትም መፍጠር የተፈቀደ ነው |

| | | |
|---|---|---|
| የድርጅቶች ዓላማ/ የሚሰማሩበት መስክ | -በአዋጁ አንቀፅ14 ላይ የተጠቀሱት ዓላማዎች ላይ ብቻ መሰመራት የተፈቀደ ነው<br>• የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ብቻ በሰብዓዊ መብት ፣ የፆታ እኩልነት ፣ የህፃናት መብት ፣ የአካል ጉዳተኞች መብት፣ የመቻቻል ጉዳዮች እና የህግ ነክ ጉዳዮች ላይ መሰማራት ይችላሉ | • ህጋዊ እስከሆነ ድረስ ምንም አይነት የዓላማ ገደብ የለውም<br>• ድርጅቶቸ በኢትዮጵያም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ አሊያም በክልሎች እና በሀገር ዓቀፍ እንዲሁም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ መንቀሳቀስ ይቻላሉ።<br>• ከማንኛውም ህጋዊ ምንጭ ያለምንም ገደብ ገቢ መሰብሰብ ይችላሉ |
| ሀገር በቀል ድርጅቶች ምዝገባ በተመለከተ | የአዋጅ ቁጥር 621/2009 አንቀፅ 68 | • በ30 ቀናት ውስጥ ምዝገባ ይከሄዳል<br>• የመመስረቻ ቃለ ጉባኤ፣ፎቶ፣ የመስራቾች መታወቂያ፣ ስምና መለያ ምልክት (ካለ) ፣ የመተዳደሪያ ደንብ፣ ዓላማ እና የሚንቀሳቀሱበት ክልሎች እና በኤጀንሲው የሚቀርብ ፎርምን መሙላት |
| የውጭ ድርጅቶችን ምዝገባ በተመለከተ | የአዋጅ ቁጥር 621/2009 አንቀፅ 68 | • በ45 ቀናት ውስጥ ምዝገባ ይከሄዳል<br>• በአግባቡ የተረጋገጠ መቋቋሙን የሚያሳይ ሰነድ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰራ የተረጋገጠበት ሰነድ፣ የተረጋገጠ የውክና ሰነድ፣ ከኤምባሲ ወይም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የድጋፍ ደብዳቤ፣ ከ2 ዓመት ላላነሰ ጊዜ የሚተገበር የስራ ዕቅድ ያስፈልጋል |
| ፈቃድን በተመለከተ | ፈቃድና ምዝገባ የተምታቱ ሀሳቦች ነበሩ | • ኤጀንሲው ምዝገባን ብቻ ያከሄዳል<br>• በህግ ካልተደነገገ በስተቀር ፈቃድ አያስፈልግም |
| ዕድሳት | የምዝገባ ዕድሳት በየ3 ዓመቱ ይደረጋል | ምዝገባው ቋሚ ስለሆነ ዕድሳት አያስፈልግም |
| የሂሳብ አያያዝና ሪፖርትን በተመለከተ | የአዋጅ ቁጥር 621/2009 አንቀፅ 79 | -ከ200 ሺህ ብር በታች ገቢ ያላቸው ድርጅቶች የሂሳብ መግለጫ መላክ ይችላሉ<br>• ድርጅቶች ሂሳባቸውን በአምስት ወራት ኦዲት ካላደረጉ ኤጀንሲው የውጭ ኦዲተር ሊሾም ይችላል<br>• 1/3ኛ የሚሆኑት የድርጅቱ አባላት ወይም ለጋሽ ድርጅቶች ወይም ከድርጅቱ ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ያላቸው የመንግስት አካላት የሂሳብ ምርመራ እንዲደረግ ከጠየቁ ኤጀንሲው የድርጅቱ ሂሳብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ሊያዝ ይችላል<br>• የሥራ መሪዎች የድርጅቱን የእያንዳንዱን የበጀት ዓመት ዋና ዋና ክንዋኔዎች የሚያሳይ ሪፖርት የሂሳብ ዓመቱ ባለቀ በ3 ወራት ውስጥ ለኤጀንሲው ማቅረብ አለባቸው<br>• በኤጀንሲው ዘንድ የሚገኙ ማናቸውም የድርጅቶች ዓመታዊ ሪፖርቶች አሊያም ሠነዶች ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት ወይም በድርጅቱ አባላት ሲጠየቅ በማናቸውም አመቺ ጊዜ ተደራሽ መሆን አለበት<br>• ማንኛውም ድርጅት የባንክ ሂሳብ ለመክፈት በቅድሚያ ከኤጀንሲው በፅሁፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት<br>• ማንኛውም ባንክ በኤጀንሲው በተጠየቀ ጊዜ በድርጅቶች ስም የተከፈቱ የባንክ ሂሳቦችን ዝርዝርና የሂሳብ መግለጫዎችን ወዲያውኑ የመስጠት ግዴታ አለበት |

| | | |
|---|---|---|
| ግምገማንና አስተዳደራዊ ዕርምጃዎችን በተመለከተ | የአዋጅ ቁጥር 621/2009 አንቀፅ 84 | • ከመንግስት አካላት፣ ከለጋሽ ድርጅቶች ወይም ከህዝብ ከሚቀርቡ  አሊያም ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት ከሚገኙ መረጃዎች በመነሳት ኤጀንሲው ማንኛውም ድርጅት ሥራውን በህግ መሠረት እየሰራ ስለመሆኑ ምርመራ ሊያካሂድ ይችላል<br>• ምርመራ ለማከናወንም በቅድሚያ ማረጋገጥ እና የምርመራ ስራዎችም በተቻለ መጠን በፈጣን ሁኔታ እና የድርጅቶችን እንቅስቃሴ ላይ እንቅፋት በማይሆን መልኩ መሆን አለበት |
| ዕገድና ማፍረስን በተመለከተ | በኤጀንሲው ዳይሬክተር ሊፈርስ ይችላል | • በከባድ የህግ ጥሰት የኤጀንሲው ዳይሬክተር 3 ወራት ላልበለጠ ጊዜ ሊያግድ ይችላል<br>• ዕገዳውም ለቦርዱ መቅረብ የሚችል ሲሆን በቦርዱም ውሳኔ ቅሬታ ካለ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይቻላል<br>• አስተዳደራዊ ዕርምጃዎች<br>○ ማስጠንቀቂያ<br>○ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ<br>○ ዕግዳን<br>○ በቦርዱ ውሳኔ መፍረስን ያካትታል<br>ፍትሐዊ የሆነ የመሰማት መብትም አላቸው |
| ይግባኝ የማለት መብትን በተመለከተ | ይግባኝ የማለት መብት የተሰጠው ለኢትዮጵያ በጎ አድራጎቶች እና ማህበራት ብቻ ነው | ማንኛውም ድርጅት የኤጀንሲውንም ሆነ የቦርዱን ውሳኔዎች ፍ/ቤት ይግባኝ የማለት መብት አለው |
| ገቢ ማሰባሰብን እና አጠቃቀምን በተመለከተ | • ከድርጅቱ ዓላማዎች ጋር በቻ በተያያዙ መስኮች ላይ ገቢ ማሰባሰብ ይቻላል። ሆኖም አስተዳደራዊ ወጪዎችን መሸፈን አይቻልም<br>• አስተዳደራዊ ወጪዎችም ከበጀቱ 30 ከመቶ መብለጥ አይችሉም። በተጨማሪም አስተዳደራዊ ወጪዎች የፕሮግራም ወጪዎችን፣ የአስልጣኞች ክፍያን እና የማማከር ክፍያዎችን የመሳሰሉትን ያጠቃልላሉ። | • ድርጅቶች ገቢ ለማግኘት በማንኛውም የንግድ እንቅስቃሴ መሰማራት ይችላሉ።<br>ሆኖም ሂሳቡን ለብቻ መያዝ ይጠበቅባቸዋል<br>• ለህዝብ አሊያም  ለ3ኛ ወገን ጥቅም የተቋቋሙ ድርጅቶች አስተዳደራዊ ወጪዎች ከ 20 በመቶ መብለጥ አይችሉም<br>• አስተዳደራዊ ወጪዎችም በጠባቡ የተተረጎሙ ሲሆን በግልፅም እንደተቀመጠው የፕሮጀክቶችን ወጪዎች አያካትቱም። |
| የራስ አስተዳደር | አዋጅ ቁጥር 621/2009 የራስ በራስ አስተዳደርን አላካተተም | • ኤጀንሲው ድርጅቶችን የመደገፍ እና ወደራስ አስተዳደር እና ተጠያቂነት ማዕቀፍ ውስጥ የማስገባት ኃላፊነት አለበት<br>• የሚቋቋመው የድርጅቶች ም/ቤትም የመመሪያ ደንብ የማውጣት እና የማስከበር ዘዴዎችን፣ ዘርፉን በቦርዱ ውስጥ እንዲወክል እና ኤጀንሲውንም በምዝገባ ስርዓት እና የመቆጣጠር ጉዳዮች ላይ እንዲያማክር ስልጣን ተሰጥቶታል። |
| ለድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ ስለማድረግ | ከሰብዓዊ መብት፣ ዴሞክራሲ፣ ስርዓተ ፆታ፣ የህፃናት መብት፣ የአካል ጉዳተኞች መብት፣ በመቻቻል ዙሪያና በህግ ጉዳይ ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች ከ10 ከመቶ በላይ በጀታቸውን ከውጭ ማግኘት አይችሉም። | • ለህጋዊ ዓላማ እና የገቢ ምንጩም ህጋዊ እስከሆነ ድረስ ምንም አይነት ገደብ የለውም<br>• የውጭ ድርጅቶች ለሀገር በቀል ድርጅቶች የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ<br>• የድርጅቶችም ፈንድ በአዋጁ ተቋቁሟል። ይህም በጎ ፈቃደኝነትንና በተጋላጭ ቡድኖች ላይ የሚሰሩ ድርጅቶችን ለመደገፍ ታስቦ የወጣ ነው። |

# ምዕራፍ 2

## የተፈፃሚነት ወሰን

# ምዕራፍ 2

# የተፈፃሚነት ወሠን

**ያስታውሱ:-**
አዲሱ አዋጅ የሚከተሉት ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል

- የውጭ ሲቪል ማህበረሰብ ድረጅቶች
- ከአንድ ክልል በላይ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሀገር በቀል ድርጅቶች
- በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ የሚንቀሳቀሱ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች

እርስዎ የሚሰሩበት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት አዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ቢሮ ካለው አሊያም ከአንድ በላይ ክልል ውስጥ የሚንቀሳቀስ ከሆነ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ሪፓርት ሊደረግ እና ምዝገባ ማካሄድ ይኖርበታል፡፡

ድርጅቶች በአንድ ክልል በቻ ከሆነ የሚንቀሳቀሰው፤ የመመዝገብ ስልጣን ባለው የክልሉ የመንግስት አካል ምዝገባ ማካሄድ አለበት፡፡ በአብዛኛው ክልሎች ይህ ስልጣን የክልሉ የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አሊያም የክልሉ ጠቅላይ ዓቃቢ ሕግ ነው፡፡

በክልሎች ህገ-መንግስት ላይ እንደተገለፀው በክልል ፓርላማዎች የሚወጡ ህጎች ከፌደራል ህጎች ጋር መፃረር የለባቸውም፡፡ ስለዚህም ክልሎች ከአዲሱ አዋጅ ጋር የሚጣጣም ህግ አውጥተው ለህገ-መንግስታዊው የመደራጀት መብት ሙሉ እውቅና እንደሚሰጡ ይጠበቃል፡፡

አዋጁ በሃይማኖት ተቋማት ላይ ተፈፃሚ አይደለም፡፡ ምክንያቱም አዋጁ የሃይማኖት ተቋማት ለሃይማኖታዊ ስርዓት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይ ተፈፃሚ ስለማይሆን ነው፡፡ የሃይማኖት ተቋማት የበጎ አድራጎት እንቅስቃሴ ላይ መሳተፍ የሚፈልጉ ከሆነ ደግሞ ራሱን የቻለ ገለልተኛ የሲቪል ድርጅት ማቋቋም አለባቸው፡፡ ይህም ድርጅት በኤጀንሲው ተመዝግቦ በአዋጁ የህግ ማዕቀፍ ውስጥ መግባት አለበት፡፡

የሃይማኖት ተቋማት ምዝገባቸውና እና አሰራራቸውን የሚሸፍን የህግ ማዕቀፍ እስኪወጣ ድረስ በአሁኑ ሰዓት በሰላም ሚንስቴር ስር ነው ምዝገባቸው የሚካሄደው፡፡

**ያስታውሱ፡-**
**አዋጁ የሚከተሉት ተቋማት ላይ ተግባራዊ አይሆንም፡፡**

- የሃይማኖት ተቋማት
- እቁብ እና እድር የመሳሰሉት ሌሎች ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ተቋማት
- የንግድ ቻምበሮች፣ የንግድ ህብረቶች፣ የዘርፍ ማህበራት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም ሌሎች በሌላ የህግ ማዕቀፍ የተሸፈኑ ማህበራት

# ምዕራፍ 3
# የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ

# ምዕራፍ 3

# የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ

## 3.1 የኤጀንሲው አላማዎች

አዋጁ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲን ሲያቋቁም መሰረታዊ አላማው ሕገ-መንግስታዊ ጥበቃ ያገኘውን የመደራጀት መብት ማረጋገጥ ሲሆን፤ በተመሳሳይ ተጠያቂነትን ማስፈንና የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት ማሳደግ ነው፡፡ ስለሆነም የኤጀንሲው አላማ ድጋፍ መስጠት እና መቆጣጠር ነው፡፡በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ ሲቪል ድርጅቶች ምቹ የምዝገባና የስራ ሁኔታን መፍጠር፤ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን አቅም ማሳደግ፤ የበጎ ፍቃደኝነት ባህልን ማበረታታት እና በሲቪል ድርጅቶችና በመንግስት አካላት መካከል ምቹ የስራ ግንኙነትን በሚያስችል ሁኔታ ማሳለጥ የኤጀንሲው የማስቻል ወይም የድጋፍ አላማዎች የሚያዛቸው ዝርዝሮች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ውስጥ ግልፅነት፤ ተጠያቂነት እና ተሳትፎን የሚያረጋግጥ የውስጥ መተዳደርያ ስርዓት እንዲኖራቸው ማስቻል፤ በሲቪል ደርጅቶች ማህበረሰብ ዘንድ የራስ ቁጥጥርን ማሳደግ እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚሰሯቸው ስራዎች የማህበረሰቡን የላቀ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ መሆናቸውን መቆጣጠር የኤጀንሲው የቁጥጥር አላማዎች ከሚያካትቷቸው ዝርዝሮች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ኤጀንሲው አሁን ያለው የተቆጣጣሪነት እና የድጋፍ ዓላማ ቀድሞ በነበረው ሕግ ላይ ካለው የተቆጣጣሪነት እና የቀጭነት አላማ ፈፅሞ የተለየ ነው፡፡

በመሰረታዊነት ኤጀንሲው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ምዝገባ ቀላል እና ፈጣን በማድረግ፤ በድርጅቶች ውስጥ እና በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የራስ አስተዳደር አቅምን በማሳደግ ብሎም በፌደራል እና በክልል መንግስታት እና በሲቪል ድርጅቶች መካከል መልካም የስራ ግንኙነትን በማሳደግ፣ የመደራጀት መብት እንዲዳብር የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡ የኤጀንሲው የተቆጣጣሪነት አላማ የሚሳካው፤ ኤጀንሲው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ተግባር እና የፋይናንስ ሪፖርት በመከታተልና በመቆጣጠር፤ የተለያዩ ብልሹ አሰራሮችን በመመርመር አስፈላጊ የሆነውን አስተዳደራዊ እርምጃዎችን በመውሰድ እንዲሁም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ም/ቤት የሚያወጣቸውን የስራ ደንብ እንዲተገበሩ በመርዳት ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ግን ኤጀንሲው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚቀርብባቸውን ክሶች የመከላከልና የመሰማት፤ በውሳኔዎችም ላይ ይግባኝ የመጠየቅ መብታቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፡፡

## 3.2 የኤጀንሲው ስልጣንና ሃላፊነት

የኤጀንሲው ስልጣንና ሃላፊነት በአዋጁ አንቀፅ 6 ላይ ተዘርዝሮ ይገኛል እነዚህም፤ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ምዝገባ፤ ክትትል እና ቁጥጥር፤ የጥናትና የሰነድ ጥንቅር፤ የማስተዳደር እና የማገዝ፤ እንዲሁም ተጨማሪ አስተዳደራዊ ስራዎች ጋር የተገናኙ ተግባራትን ያካትታል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ስለ ምዝገባና ቁጥጥር ከላይ በክፍል 3.1 ተብራርተዋል፡፡

የኤጀንሲው የጥናትና ሰነድ ጥንቅር ሃላፊነት ኤጀንሲው በራሱ እና በክልል መንግስታት ተመዝግበው በሃገሪቱ ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን ድርጅቶች ቁጥር፣ የተሰማሩባቸውን አካባቢዎች፣ የተጠቃሚዎችን አይነትና የመሳሰሉትን መረጃዎች የሚይዝ የመረጃ ቋት/ማእከል የማቋቋም፤ ብሎም መረጃዎቹን መደበኛ የህትመት ሚድያዎችንና የበይነ መረብን በመጠቀም የማሳተም ተግባራትን ያጠቃልላል። የመረጃ ቋቱ/ማእከሉ ለጥናት አጥኚዎች፣ ለምሁራን፣ ለሚድያ ባለሙያዎች እና ለፖሊሲ አመንጪዎች ጨምሮ ለህዝብ ክፍት መሆን አለበት። ከዚህ በተጨማሪ ኤጀንሲው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በልማት እና በዴሞክራሲ ግንባታ ዙሪያ ያላቸውን ሚና አስመልክቶ ጥናቶችን በማጥናት እና በመተንተን፤ በዘርፉ ላይ የሚታዩ ለውጦችን፣ ተግዳሮቶችን እና መልካም አጋጣሚዎችን በመለየት፤ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ማገዝ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መንግስትን ያማክራል።

የኤጀንሲው የማስተባበር ሃላፊነት፤ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የልማት ተግባራት ከመንግስት የልማት እቅዶች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ መመሪያ የማዘጋጀት ሚናን ያካትታል። ይሄም በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና በመንግስት መካከል መጣጣምን ለመፍጠር እንጂ፤ በምንም አይነት መልኩ ኤጀንሲው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በልማት ዙሪያ የሚያከናውኑትን ተግባራት ይወስናል ማለት አይደለም። መመሪያዎቹም የማማከር ተግባር ያላቸውና ጠቅለል ያሉ እንጂ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አላማዎች እና ተግባራት፤ የትኩረት አቅጣጫዎችንና የስራ መተግበሪያ መንገዶችን የመወሰን ነፃነታቸውን ሊገድብ አይገባም።

ሌላው ከኤጀንሲው የማስተባበር ሃላፊነት ጋር የሚገናኘው የኤጀንሲው ተግባር የዘርፍ አስተዳዳሪዎችን ጨምሮ በፌደራልና በክልል የመንግስት ተቋማት እና በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መካከል ትብብር እንዲኖር ማሳለጥ ነው። ይህም በዋናነት የሚከናወነው አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠትና የጋራ ምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት ነው። መሰል የምክክር መድረኮች የስራ ችግሮችን ከመፍታት ባለፈ የጋራ አቅድ፣ የልማት ግምገማ፣ የእውቀት ሽግግር፣ በስሯቸው ስራዎች ላይ ግብረ መልሶች የሚያገኙበት፣ የምርጥ ተሞክሮዎች እና ፖሊሲዎች መማማሪያ መድረኮች ናቸው። ስለሆነም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የጋራ የምክክር መድረኮችን የመንግስት ፖሊሲዎችና ስራዎች፤ የሲቪል ድርጅቶች የሚወክሏቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች ጨምሮ የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ እንዲሆን ተፅእኖ ለመፍጠር ሊጠቀሙባቸው ይገባል።

ኤጀንሲው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሲፈርሱ በሂሳብ አጣሪነት የሚያገለግሉ ባለሙያዎችን ዝርዝር የማዘጋጀትና ስራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን የመቆጣጠር ሃላፊነት አለበት። ከዚህ በተጨማሪ ኤጀንሲው የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድን የማስተዳደር ሃላፊነትም አለበት። ይህም (የኤጀንሲው የሲቪል ማህበረሰብ ፈንዱን የማስተዳደር ሃላፊነት) በቀደመው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ኤጀንሲው ተሰጥቶት ከነበረው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ያለምንም መመርያ እና ተቋማዊ ብቃት/ችሎታ የማፍረስ ስልጣን፤ በአሁኑ አዋጅ ከተቀመጠው ሂሳብን የማጣራት እና ንብረት የማስተዳደር ሃላፊነት ፍፁም የተለየ ነው። የአሁኑ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሕግ ድርጅቶች የማፍረስ ስልጣን የሰጠው ለፍ/ቤቶች ሲሆን በተወሰኑ ሁኔታዎች ብቻ የኤጀንሲው ቦርድ ይሄ ስልጣን ይኖረዋል። ከዚህ በተጨማሪም በአዋጁ መሰረት ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት መፍረስ በኋላ የድርጅቱ ንብረቶች፤ እንደ ንግድ ተቋም፤ በባለሙያ  የሂሳብ አጣሪ አደራ ስር ይሆናሉ። በዚህ ረገድ የኤጀንሲው ስልጣን የሂሳብ አጣሪውዎችን ዝርዝር ማዘጋጀትና አነሱንም የመቆጣጠር ብቻ ይሆናል።

አዲሱ አዋጅ ካስተዋወቃቸው መልካም ነገሮች ውስጥ በኤጀንሲው የሚተዳደር የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ መቋቋሙ ነው። በአዋጁ አንቀፅ 86 እንደተጠቀሰው፤ የፈንዱ ገቢ ምንጮች በአሁኑም ሆነ በቀድሞ አዋጅ ከፈረሱ ድርጅቶች የሚገኙ ንብረቶች እና ከመንግስት ድጎማ ይሆናል። ኤጀንሲውም ፈንዱን በውስን ሃብት ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን የማህበረሰብ ስራዎች ለሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እንደሚደለድል ይጠበቃል። የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ አስተዳደርን በተመለከተ ኤጀንሲው ዝርዝር ህጎችን ያወጣል።

ከላይ ከተመለከትናቸው ኤጀንሲው ስልጣኖች በተጨማሪ፤ ኤጀንሲው በዘርፉ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በቅርበት የመስራት፤ የበጎ ፈቃደኝነትን ባህል የማበረታታትና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን መተዳደሪያ ደንቦችና ማሻሻያዎችን የማረጋገጥ እና የመመዝገብ ሃላፊነት አለው። የኤጀንሲው ዋና የስራ እንቅስቃሴ በአዲስ አበባ ቢሆንም፤ ኤጀንሲው በክልል ከተሞች ቅርንጫፎቹን በመክፈት ወይም አገልግሎቶቹን የክልል አካላትን በመወከል ተደራሽ እንደሚያደርግ ይጠበቃል።

## 3.3 የኤጀንሲው አደረጃጀት

ኤጀንሲው በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና በመንግስት ተወካዮች የተዋቀረ ቦርድ እና በዋና ዳይሬክተርና በምክትሉ የሚመራ አስተዳደር ይኖረዋል።

### 3.3.1 ቦርዱ

ቦርዱ በሶስት የመንግስት መስሪያ ቤት ተወካዮች፣ በሰባት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ተወካዮች እና በአንድ ባለሙያ የተዋቀረ ነው። ባለሙያው እና ሶስቱ የመንግስት ተወካዮች በጠቅላይ አቃቢ ህግ የሚሾሙ ሲሆን፤ ከሰባቱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ተወካዮች ውስጥ ሶስቱ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ም/ቤት ሲመረጡ ቀሪዎቹ ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት ብሄራዊ ፌደሬሽን እና ከሴቶችና ወጣቶች ማህበራት ሁለት ሁለት አባላት ይወከላሉ። የቦርዱ ሊቀ መንበር በጠቅላይ አቃቢ ህግ ይሾማል። የቦርዱ አባላት የስራ ዘመን ሶስት አመት ሲሆን ለአንድ ተጨማሪ ዘመን ዳግም መመረጥ ይችላሉ። ነገር ግን፤ ቀጣይነትንና ተቋማዊነትን ለማስቀጠል፤ ከመንግስትና ከሲቪል ድርጅቶች አንድ አንድ ተወካይ በአጠቃላይ ሁለት ተወካዮች የሥራ ዘመን አራት አመት ሊሆን ይገባል። ሆኖም ግን እነዚህ ተወካዮች ዳግም ሊመረጡ አይችሉም (አንቀፅ 10(3))።

ቦርዱ ከኤጀንሲው አላማ ጋር የሚጣጣም ኤጀንሲው የሚመራባቸውን የፖሊሲ አቅጣጨዎች የማስቀመጥ፤ የኤጀንሲውን እቅድ እና ሪፖርት መርምሮ የማፅደቅ፤ በኤጀንሲው የሚሰጡ የህግ ትርጓሜዎችን የመከታተል እና የመቆጣጠር፤ የምዝገባ ክልከላ እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እገዳን ጨምሮ በኤጀንሲው ዳይሬክተር የሚሰጡ ውሳኔዎችን መሠረት አድገው የሚቀርቡ ይግባኞችን የመመርመር፤ ከባድ የህግ ጥሰቶች ሲፈፀሙ ወይም መሠል የህግ ጥሰቶች ላይ የማስተካከያ እርምት ሳይወሰድ ሲቀር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የማፍረስ እና አዋጁን ለመተግበር የሚያስችል መመርያ የማውጣት ስልጣን አለው፡፡

## 3.3.2 ዳይሬክተሩና ምክትል ዋና ዳይሬክተር

ዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ አቃቤ ህግ ሆኖ ከቦርዱ ከሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የኤጀንሲውን ስራዎች ይሰራል፡፡ ኤጀንሲው ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ማንኛውም ግንኙነቶች ላይ በዳይሬክተሩ ይወክላል፡፡ ዳይሬክተሩ የኤጀንሲውን አመታዊ የስራ እቅድ እና በጀት፤ የስራ አፈፃፀም እና የሂሳብ ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡ በተጨማሪም ዳይሬክተሩ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፡፡ ኤጀንሲው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምዝገባ እና ስራዎች ዙሪያ ባለው ስልጣን ላይ ዳይሬክተሩ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ ይሆናል፡፡ ስለሆነም በኤጀንሲው ሬጅስትራር ወይም የቁጥጥር እና ክትትል ሃላፊ የሚሰጡ ውሳኔዎች፤ እንደየጉዳዩ ለሚመለከተው የቡድን መሪ፣ የሬጅስትራር ሃላፊ ወይም ተቆጣጣሪ ዳይሬክተር፤ በመጨረሻም ለዋና ዳይሬክተር ይግባኝ ሊቀርብ ይችላል፡፡

ምክትል ዳይሬክተሩ የኤጀንሲውን ተግባራት በማቀድ፣ በማስተባበር እና በመምራት ዳይሬክተሩን ይረዳል፤ ዋና ዳይሬክተሩም በማይኖርበት ጊዜ ዳይሬክተሩን ተክቶ ይሰራል፡፡

# ምዕራፍ 4
# ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምስረታ እና ምዝገባ መርሆዎች

# ምዕራፍ 4

# ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምስረታ እና ምዝገባ መርሆዎች

## 4.1 የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚቋቋሙበት መርሆዎች

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የበጎ ፈቃደኛ ሰዎች ማህበር ሲሆን አባላቶቹ ጠቃሚ ብለው ላሰቡትና ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ነው። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን አመሠራረትን የሚመሩ መሰረታዊ መርሆዎች በአዋጁ አንቀፅ 16 የተዘረዘሩ ሲሆን፤ በዚሁ አንቀፅ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መገለጫ የሆኑት በጎ ፈቃደኝነትና ለትርፍ ያልተቋቋሙ መሆናቸው አፅዕኖት ተሰጥቶታል።

በዚህ ረገድ አንቀፅ 16(2) በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ውስጥ አባልነት በጎ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያስረግጣል። ይህም ማለት በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ውስጥ መግባትም ሆነ መውጣት የሰዎች ፈቃድ ወይም ምርጫ ላይ የተመሠረተ ነው፡፤ በዚህ መሠረት አንድ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት አባል በአባልነቱ ያለፈቃዱ ተገዶ ሊቆይ አይችልም።

በህጉ ላይ በሁለተኛነት የምናገኘው መርሆ ከአድሎ የፀዳ አሰራርን ነው። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ቅቡልነት ያላቸው የአባላት መቀበያ መስፈርቶችን የመወሰን መብት ሲኖራቸው እነዚህ መስፈርቶች የዘፈቀድ ሳይሆኑ ህጋዊና ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አላማ ጋር የሚሄዱ መሆን አለባቸው። በዚህ መሰረት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በእድሜ፣ በፆታ፣ በዘር፣ በአካል ሁኔታ፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በሃይማኖት፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚ መደብን መሠረት ያደረገና ልዩነት የሚፈጥር የአባልነት መስፈርት ሊኖራቸው አይገባም። ይህ ማለት ግን የሙያ ማህበራት ወይም የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍል ማህበራት ለምሳሌ፡ የወጣቶች፣ የሴቶች ወይም የአረጋዊያን ማህበራት፤ የተለየ የአባልነት ወይም የተሳትፎ ደረጃ አይኖራቸውም ማለት አይደለም። ለምሳሌ፡ በሴቶች ማህበር ወንድ አባላት በተባባሪ አባልነት ደረጃ ሊኖሩት የሚችሉ ቢሆንም ሙሉ አባል ግን ላይሆኑ ይችላሉ። ይህ በተመሳሳይ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለወጣቶችና ለአረጋውያን ወይም ለሙያ ማህበራትም የሚሰራ ነው። እንደነዚህ አይነት ማህበራት የአባላቶቻቸውን ወይም የተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል ጥቅም የማስጠበቅ አላማን አንግበው የተቋቋሙ ስለሆኑ የአባልነት መስፈርታቸው ከተቋቋሙበት አላማ ጋር የሚሄድ መሆን አለበት።

በሶስተኛነት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች መሆናቸው ነው። ይህ ማለት ግን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አላማቸውን ለማሳካት የሚረዱ ገቢ ማመንጫ ስራዎች ወይም የንግድ ስራ ውስጥ አይሳተፉም ማለት አይደለም። ድርጅቶቹ የሚያገኙትን ትርፍ ተከትሎ በአባላት መካከል የትርፍ ክፍፍል እስከሌለና ገቢው የድርጅቶቹን የስራ እንቅስቃሴ ወይም አስተዳደራዊ ወጪ ለመሸፈን እስከዋለ ድረስ ህጉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ማንኛውም ህጋዊ የገቢ ማግኛ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ ይፈቅዳል። በድርጅቶቹ የሚከናወነው ንግድ እራሱን የቻለ የሂሳብ መዝገብ ሲኖረው፤ አግባብነት ባላቸው የንግድ እና የታክስ ህግ ማዕቀፎች ይገዛል።

አራተኛ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የውስጥ አስተዳደር የዴሞክራሲ መርሆዎች ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። አባላት ድርጅቱን የሚመለከት ማንኛውም ወሳኝ ጉዳይ ላይ በመተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው የስብሰባ ስነስርዓት መሠረት በጉዳዩ ላይ የመምከር መብት አላቸው። በውሳኔም ሂደቶች ላይ እያንዳንዱ አባል እኩል ድምፅ የሚኖረው ሲሆን፤ በመተዳደሪያ ደንብ ላይ ይህን የሚፃረር ማንኛውም ድንጋጌ ተፈፃሚነት አይኖረውም። አባላት ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱ የአመራርነት ስፍራ (ለቦርድ፣ ጠቅላላ ጉባኤ እና ሌሎች የኮሚቴ ቦታዎችን ጨምሮ) የመምረጥ ብሎም የመመረጥ መብት አላቸው። አባላት የድርጅቱን የኦዲት ሪፖርት፣ ቃለ ጉባዔ፣ የስራ እና የሂሳብ ሪፖርቶችን ብሎም የስራ እቅድን ጨምሮ ተጨማሪ አስፈላጊ ሰነዶችን የማግኘትና መረጃን መሠረት ያደረገ ውሳኔ የመስጠት መብት አላቸው። በሌላ አነጋገር በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ውስጥ የውሳኔ ሂደት ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሁም አሳታፊ መሆን አለበት።

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ከላይ የተመለከትናቸውን መርሆዎች በመተዳደሪያ ደንባቸው ሊያካትቱና ለመርሆዎቹም መገዛት አለባቸው።

## 4.2 የምዝገባ ሂደት

በአዋጁ ብሎም በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ አሰራር መሠረት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የምዝገባ ሂደት ሶስት ደረጃዎች አሉት። እነዚህም የመነሻ ደረጃ፣ የሰነድ ጥንቅር ደረጃ እና የምዝገባ ወይም የማፅደቅ ደረጃ ናቸው። ከዚህም ጋር በተያያዘ መታወቅ ያለበት ነገር እነዚህ የምዝገባ ሂደቶች፤ ያለምንም ምዝገባ እንደ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት መንቀሳቀስ የሚችሉትን የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎች ላይ የማይሰራ መሆኑን ነው። ከዚህ በተጨማሪም ለምዝገባ ጥያቄ እንዳቀረበው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት አይነት (አገር በቀል/የውጭ ድርጅት ወይም ማህበር/ቦርድ - መር/የዘለቄታ/የአደራ/ህብረቶች) ፤ በእያንዳዱ የምዝገባ ደረጃ ላይ የሚከወኑ ተግባራት ይለያያሉ።

በመጀመሪያው የመነሻ ደረጃ አንድ ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም ተመሳሳይ አላማ ያላቸው ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በወል/በጋራ በኢትዮጵያ ህግ መሠረት  የሲቪል ድርጅት ለማቋቋም የሚወስኑበት ወይም ቀድሞ የተመሰረተ የውጭ ድርጅት  በኢትዮጵያ ለመመዝገብ የሚወስኑበት ደረጃ ነው። ለሃገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መስራቾቹ የድርጅቱን አላማ መለየት እና የድርጅቱን አወቃቀር መምረጥ ይኖርባቸዋል። መስራቾቹ ድርጅቱን ከማቋቋማቸው አስቀድመው የቅድመ ዝግጅት ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፤ ከነዚህም ስራዎች መካከል፡ አባላትን ስለ ማህበሩ ማሳወቅ (ለምሳሌ፡ ማህበራን) ፤ ሸሪክ ሊሆኑ የሚችሉ ማህበራትን ማጥናት (ለምሳሌ፡ ለህብረቶች)። መስራቾቹ የቅድመ ዝግጅት ስራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የመስራቾች ጉባኤ ወይም የቦርድ ስብሰባ ወደ መጥራት ይሻገራሉ።

በቀጣዩ የሰነድ ጥንቅር ደረጃ መስራች አባላት በአዋጁና በኤጀንሲው መመሪያዎች ላይ አስፈላጊ ናቸው ተብለው የተዘረዘሩ በርካታ ሰነዶችን መዝግበው ለኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ የሚመዘገበው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት የቱንም አይነት ቢሆን ሁሉም በምዝገባ ሂደት ውስጥ የሚያስፈልጉ ድርጅቶች የመመስረቻ ጉባዔ ወይም የመስራቾች ስብሰባ ማካሄድ አለባቸው፡፡ በዚህ ሂደት መስራቾች ለጉባኤው ወይም ለስብሰባው ረቂቅ የመመስረቻ ፅሁፍ ለማፀደቅ ማቅረብ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም መስራቾች የስብሰባውን ወይም የጉባኤው ቃለ ጉባዔ የመመዝገብ ግዴታ ሲኖርባቸው፤ ቃለ ጉባኤውም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱን ስም፤ ዓላማ፤ አድራሻ፣ የስራ እቅድ፣ የዋና መ/ቤት አድራሻ፣ የቦርድ አባላትን ዝርዝር፣ የዳይሬክተር ሹመት፣ አርማ (ካለ) ዝርዝር መያዝ አለበት፡፡ ከላይ ለተመለከትናቸው በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከሚፀድቅ የመመስረቻ ፅሁፍ እና የመስራቾች ጉባዔ ወይም የስብሰባ ቃለ ጉባዔ እና መተዳደሪያ ደንብ ባለፈ ኤጀንሲው የምዝገባ ማመልከቻ በሚቀርብበት ወቅት ሁሉም የቦርድ አባላት እና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቱ ዳይሬክተር በአካል እንዲቀርቡ ወይም በአግባቡ በተወከለ ወኪል ተወክለው እንዲቀርቡ ያስገድዳል፡፡ የምዝገባው ማመልከቻ የእያንዳንዱ የቦርድ አባል እና የዳይሬክተሩ ጉርድ ፎቶ ግራፍ እና የመታወቂያ ኮፒ ማካተት አለበት፡፡

አጀንሲው ከሚጠይቃቸው መደበኛ ሰነዶች በተጨማሪ እንደ ድርጅቶቹ ድርጅታዊ አወቃቀር ተጨማሪ ሰነዶች ይጠየቃል፡፡ በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ሆነው መመስረት የሚሹ የሙያ ማህበራት መስራቾች ብቃት/ችሎታን የሚያስረዳ የሙያ ወይም የትምህርት ሰነድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ የህብረት ወይም የህብረት ህብረት መስራች የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የእያንዳንዱን የህብረት አባላት ከኤጀንሲ የተሰጣቸውን የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለባቸው፡፡

በመጨረሻም ከላይ የተመለከትናቸው ሰነዶች በሙሉ ተሟልተው ለኤጀንሲው ከቀረቡ በኋላ፤ ኤጀንሲው አመልካች ድርጅት አግባብነት ባለቸው ህጎች የተቀመጡ መስፈርቶች ሟሟላቱን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆነውን ምርመራ ያደርጋል፡፡ ምርመራው ለሃገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች 30 ቀን ለውጭ ድርጅቶች ደግሞ እስከ 45 ቀን ሊወስድ ይችላል፡፡ ምርመራውንም ተከትሎ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶቹ ምዝገባ ሊፈቀድ ወይም ሊከለከል ይችላል፡፡ በአንቀፅ 57(3) መሠረት ኤጀንሲው ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ለአመልካች የምዝገባ የምስክርነት ወረቀት ያልሠጠው እንደሆነ፤ አመልካች የጊዜ ገደቡ ካለቀ በኋላ ባሉ 30 ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው ቦርድ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ ቦርዱ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በ60 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ አመልካች ዳግም በቦርዱ ውሳኔ ቅሬታ ካደረበት የቦርዱ ውሳኔ ከደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡ ድርጅቱ አንዴ ከተመዘገበ በኋላ ሙሉ ሕጋዊ ሰውነት ያገኛል፡፡

# ምዕራፍ 5
# የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አይነቶች

# ምዕራፍ 5

# የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አይነቶች

ማህበር ፣ ቦርድ መር ድርጅት፣ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት፣ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት፣ የበጎ አድራጎት ኮሚቴ

እንደሚያስታውሱት የቀድሞ አዋጅ ድርጅቶችን ከገቢ ምንጭ አንፃረ (የኢትዮጵያ ነዋሪዎች እና የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት)፣ ከዓላማ/ተጠቃሚዎች አንፃር (ለአባላት ወይም ለሶስተኛ ወገን)፣ በአወቃቀር (በጎ አድራጎት፣ ማህበራት፣ የዘለቄታ በጎ አድራጎት፣ የአደራ በጎ አድራጎት፣ የበጎ አድራጎት ኮሚቴ) እና ከተቋቋመበት ሀገር አንፃር (የውጭ ድርጅቶች እና የኢትዮጵያ/የነዋሪዎች በጎ አድራጎት) የሚሉ ክፍፍሎች ነበሩ። ይህ ቢሆንም በአዲሱ አዋጅ የመደራጀትን መብት ያለአግባብ የሚገድቡ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ክፍፍሎች አስቀርቷል። ከገቢ ምንጭ አንፃር ተደርጎ የነበረው ክፍፍል ደግሞ ከሰብዓዊ መብት፣ የፆታ እኩልነት፣ አካል ጉዳት፣ የህፃናት መብት፣ ዴሞክራሲ እና የግጭት አፈታት ዙሪያ ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች ላይ ህገ-መንግስታዊ የሆነውን የመደራጀት መብት አግባብ ያልሆነ የገንዘብ እገዳ በማድረግ የጣሰ ነበር። በበጎ አድራጎት እና በማህበራት መካከል የነበረው የተሳሳተ ክፍፍል ድርጅቶች ለአባላት እና ለህብረተሰቡ ወይም ለተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል ማለትም የሞያ ማህበራትን እንደአስረጂነት ብንወስድ አባላቶቻቸው ለህብረተሰቡ ያላቸውን ሚና በማበልፀግ እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ የአባሎቻቸውን አቅም በመገንባት አንድነታቸውን ማረጋገጥ እንደሚችሉ ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ነበር።

ስለዚህም አዲሱ አዋጅ ከአወቃቀር እና ከተቋቋሙበት ሀገር አንፃር ድርጅቶችን እንደሚከተለው ከፋፍሏቿል።

## 5.1 የውጭ እና ሀገር በቀል ድርጅቶች

### 5.1.1 የውጭ ድርጅቶች

የውጭ ድርጅቶች ማለት በውጭ ሀገራት የተቋቋሙ እና በኢትዮጵያ በተመዘገበ የቅርንጫፍ ቢሮ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ናቸው። አዲሱ አዋጅ የፋይናንስ እና የቴክኒክ ድጋፍ ለሀገር በቀል ድርጅቶች ወይም ለሌሎች ድርጅቶች ድጋፍ ለማድረግ ቅርንጫፍ መክፈት ለሚፈልጉ የውጭ ድርጅቶች ላይ የነበረውን እገዳ አስቀርቷል። ስለሆነም የውጭ ድርጅቶች ቀጥታ የሆነ ፕሮጀክት ለማስፈፀም ሆነ የቴክኒክ እና የፋይናንስ ድጋፍ ለሀገር በቀል ድርጅቶች ለማድረግ ወይም ሁለቱንም ለማድረግ ቅርንጫፍ ለማቋቋም ነፃ ናቸው። እንዲሁም አዲሱ አዋጅ ሀገር በቀል ድርጅቶች አቅም ለመገንባት ከውጭ ድርጅቶች ጋር አብረው እንዲሰሩ ያበረታታል። በሰብዓዊ መብት እና ዴሞክራሲ ዙሪያም እንዲሰሩ ተፈቅዷል። ሆኖም ለፖለቲካ ፓርቲዎች በቀጥታ ድጋፍ አሊያም ግፊት ማድረግ አይችሉም። እንዲሁም ምርጫን ለመከታተል እና የመራጮች ትምህርት ለመስጠት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

## 5.1.2 የሀገር በቀል ድርጅቶች

የሀገር በቀል ድርጅቶች ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ኢትዮጵያውያን ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪ በሆኑ የውጭ ዜጎች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቋቋሙ ድርጅቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ ነዋሪ በሆኑ የውጭ ዜጎች የሚቋቋሙ ሀገር በቀል ድርጅቶች ለፖለቲካ ፓርቲዎች ግፊት ማድረግ ባይችሉም ለትርፍ ላልሆነ ማንኛውም ህጋዊ ዓላማ የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ እስካልሆነ ድረስ የመሰማረት ሙሉ ነፃነት አላቸው፡፡ በአዋጁም አንቀፅ 62(5) ላይ እንደተገለፀው የውጭ ድርጅቶች እና የኢትዮጵያ ነዋሪ በሆኑ የውጭ ዜጎች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቋቋሙ ድርጅቶች  በሌላ ህግ ካልተፈቀደላቸው በቀር የፖለቲካ ፓርቲዎችን በማግባባትም ሆነ ግፊት በማድረግ ተፅዕኖ መፍጠር፣ በመራጮች ትምህርት ወይም በምርጫ መታዘብ ሥራ ላይ መሰማራት አይችሉም፡፡ የሀገር በቀል ድርጅቶች የሃይማኖት ተቋማትን፣ በሌላ ህግ መሰረት የተቋቋሙ ማለትም እንደ ንግድ ማህበራት፣ የንግድ ምክር ቤቶች፣ የዘርፍ ማህበራት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም ዕድር፣ዕቁብ፣ ሰንበቴ እና የመሳሰሉትን ባህላዊ ማህበራትን አያካትትም፡፡

የተለየዩ አይነት ሀገር በቀል ድርጅቶች አሉ፡፡ እነርሱም በአዋጁ አንቀፅ 18 መሰረት ማህበር፣ ቦርድ መር ፣ የዘለቄታ በጎ አድራጎት፣ የአደራ በጎ አድራጎት እና የበጎ አድራጎት ኮሚቴ ናቸው፡፡

**ማህበራት፡-** ማለት ቁጥራቸው አምስት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት የሚመሰረት እና ጠቅላላ ጉባኤው የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ አካል  የሆነበት ድርጅት ነው፡፡ ከቀድሞ አዋጅ ላይ ካለው ጋር ሲነፃፃር ማህበራት የአባሎቻቸውን መብትና ፍላጎት ለማጎልበት፣ ለጠቅላላው ማህረሰብ አሊያም ለተወሰነ የማህበረሰቡ ክፍል (ሴቶች፣ አርብቶ አደሮች፣ አካል ጉዳተኞች) ወይም አባላቱ ጠቃሚ ነው ለሚሉት ማንኛውም ዓላማ (እንደ አዕዋፋትን ለመመልከት ወይም መፅሃፍትን ለማንበብ) መቋቋም ይችላሉ፡፡

የአዲሱ አዋጅ አንቀፅ 2(1) የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ቢያንስ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች በፈቃደኝነት የሚመሠረት መንግስታዊ ያልሆነ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ከፖለቲካ ገልለተኛ የሆነ በማለት ሲገልፀው ሰው የሚለውን ደግሞ የአዋጁ አንቀፅ 2(17) ሰው ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሲል ይተረጉመዋል፡፡ ማህበራትም ሆኑ ሌሎች አይነት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በተፈጥሮ አሊያም ሕጋዊ ሰውነት ባላቸው ወይም በሁለቱም ሊመሠረቱ ይችላሉ፡፡ እዚህ ጋር ሊያስተውሉት የሚገባው ነጥብ ማህበራት አባላት መር ድርጅት መሆናቸውን ነው፡፡ ማለትም ጠቅላላ ጉባዔው የበላይ ውሳኔ ሰጪ አካል ነው ማለት ነው፡፡ ከአወቃቀር አንፃር አንዳንድ ማህበራት ከጠቅላላ ጉባዔው በተጨማሪ የስራ አመራር ቦርድ እና የአስፈፃሚ ዳይሬክተር እና አስፈላጊ ሰራተኞች አሏቸው፡፡ ሌሎች ደግሞ በፕሬዚዳንት/ ሊቀ-መንበር የሚመሩ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ ምክትል ፕሬዚዳንት/ምክትል ሊቀ-መንበር፣ ፀሃፊ፣ ገንዘብ ያዥ እና የፋይናንስ ኃላፊ  ከተለየ አመራር ወይም ፀሐፊ ውጪ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የሁለተኛው የተለመደው በአብዛኛው በወጣቶች፣ ሴቶች እና የሞያ ማህበራት ሲሆን አብዛኛው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የመጀመሪያውን አይነት አወቃቀር ይከተላሉ፡፡ በእርግጥ አዲሱ አዋጅ አወቃቀር ምን መምሰል እንዳለበት አያስቀምጥም፡፡ ነገር ግን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መተዳደሪያ ደንባቸው ላይ አወቃቀራቸውን መግለፅ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

**ቦርድ መር ድርጅቶች፡-** ማለት ቦርዱ የመጨረሻ/ የበላይ ውሳኔ ሰጪ አካል የሆነበት ድርጅት ነው። ቁጥራቸው ሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ የተፈጥሮ አሊያም ህጋዊ ሰውነት ባላቸው አካላት ሊቋቋም ይችላል። የመጀመሪያዎቹ የቦርድ አባላት በመመስረቻ ሰነዱ ላይ በመስራቾቹ ይሰየማሉ። የቦርድ አባላት የስራ ዘመንና ከምስረታ በኋላ የቦርድ አባላት የሚሰየሙበት ስርዓት በድርጅቱ የመተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል። ቦርዱ ከ5-13 የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል። ከድርጅቱ የስራ አመራሮች ጋር የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያላቸው ሰዎች የቦርድ አባል መሆን አይችሉም። ድርጅቱ ለቦርዱ ተጠሪ የሆነ ሥራ አስኪያጅ እና አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል። ዝርዝሩ በድርጀቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል።

**የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት፡-** ማለት አንድ የተለየ ንብረት፣ ገንዘብ በስጦታ፣ በኑዛዜ ወይም በኤጀንሲው ትዕዛዝ በዘላቂነትና በማይመለስ ሁኔታ ተለይቶ ለተገለፀ የበጎ አድራጎት ዓላማ ብቻ የሚውልበት ድርጅት ነው። ድርጅቱም የስራ አመራር ቦርድ፣ ስራ አስኪያጅ፣ ኦዲተርና ሌሎች አስፈላጊ የስራ ክፍሎች ይኖሩታል። ቦርዱም ቢያንስ 3 አባላት ሊኖሩት ይገባል። ቦርዱ የድርጅቱ የመጨረሻ/ የበላይ ውሳኔ ሰጪ አካል ነው።

**የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት፡-** ማለት ድርጅቱን በሚያቋቁመው ሠነድ መሠረት አንድ የተለየ ንብረት ለበጎ አድራጎት ዓላማ ብቻ እንዲውል ከ3-5 በሚደርሱ ባለአደራዎች የሚተዳደር ድርጅት ነው።

እንደዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅት በስጦታ፣ በኑዛዜ ወይም አግባብነት ባለው የመንግስት አካል ውሳኔ ሊቋቋም ይችላል። ነገር ግን የሚለየው በቦርድ ወይም በስራ አስኪያጅ ሳይሆን በባለአደራዎች መተዳደሩ ሲሆን ሌላው ደግሞ በአዋጁ አንቀፅ 33(1) መሠረት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ መቋቋም መቻሉ ነው።

**የበጎ አድራጎት ኮሚቴ፡-** ማለት ቁጥራቸው አምስት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት ለበጎ አድራጎት ዓላማ ከህዝብ ለመሰብሰብ ሀሳብ ያላቸው ሰዎች ስብስብ ነው። ይህ ስብስብ ለምሳሌ በተፈጥሮ አደጋዎች እና ለመሳሰሉት አደጋዎች ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ገንዘብ ለማሰባሰብ ሊቋቋም ይችላል። የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት የታቀደውን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ ከሆነው እጅግ የበዛ ከሆነ ወደ ዘላቂ በጎ አድራጎት ድርጅት ይቀየራል። ኮሚቴው ፕሬዚዳንት፣ ገንዘብ ያዥ እና ኦዲተር ሊኖሩት ይገባል። ኮሚቴው በኤጀንሲው ሳይፀድቅ ገንዘብም ሆነ ንብረት ማሰባሰብ ሆነ ሌሎች ማናቸውም ድርጊት መፈፀም አይችልም። ኮሚቴው ለሰበሰበው ገንዘብ የተብራራ የሂሳብ ሪፖርት ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት። ከኮሚቴው እንቅስቃሴዎች ለሚመነጩ ግዴታዎችና እንደ ማጭበርበር ላሉ ዕዳዎች አባላቱ በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊ ይሆናሉ። ይህም ማለት አንድ አባል ለኮሚቴው ዕዳ ኃላፊ ሆኖ ከከፈለ በኋላ ከሌሎች የኮሚቴው አባላት የየድርሻቸውን ሊያስከፍል ይችላል።

**ህብረቶችና የህብረቶች ህብረት፡-** አዲሱ አዋጅ ካስተዋወቃቸው ለውጦች አንዱ የህብረቶች አመሰራረት እና ስልጣን ነው፡፡ የቀድሞ አዋጅ የህብረቶች አመሰራረት እና ስልጣን ላይ የተለያዩ ገደቦችን ያስቀመጠ ነበር፡፡ ለአስረጂነት ያህል የኢትዮጵያ በጎ አድራጎቶች ከውጭ እና ከነዋሪዎች ድርጅቶች ጋር ህብረት ማድረግ አይችሉም ነበር፡፡ በጎ አድራጎቶችም ከማህበራት ጋር ህብረት መፍጠር አይችሉም ነበር፡፡ በተጨማሪም ለህብረቶች የሚደረግም ወጪ እንደአስተዳደራዊ ወጪ ተደረጎ ይቆጠር ነበር፡፡ ይህም የህብረቶችን አንቅስቃሴ እጅጉን ፈታኝ አድርጎት ቆይቷል፡፡ የህብረቶች ህብረትም እንዴት እንደሚመሰረት አዋጁ ግልፅ የሆነ ነገር አያስቀምጥም ነበር፡፡ ይህም የህብረቶችን ህብረት መመስረት የማይቻል አድርጎት ቆይቶዋል፡፡

አዲሱ አዋጅ እነዚህን እና መሰል ገደቦችን ያስወገዱ በጎ ለውጦችን አስተዋውቋል፡፡ በገቢ ምንጭ ላይም ተመርኩዞ የነበረው ክፍፍል (የኢትዮጵያ እና የነዋሪዎች ድርጅቶች እና የመሳሰሉት ክፍፍሎች) በመነሳታቸውም ህብረት የመፍጠርም ገደቦች በተግባር ተወግዶዋል፡፡ እንዲሁም የሀገር በቀል ድርጅቶች ከውጭ ድርጅቶች ጋር እና የውጭ ድርጅቶች ከሀገር በቀል ድርጅቶች ጋር ካለምንም የገቢ ምንጭ እና የስልጣን ገደብ ህብረት መፍጠር ይችላሉ፡፡

በተመሳሳይ መልኩም ማህበራትም ከቦርድ መር ድርጅቶች ጋርም ሆነ ከሌላ ተመሳሳይ ድርጅቶች ጋር ህብረት መፍጠር ይችላሉ፡፡

አዲሱ አዋጅ በህብረቶች ስልጣን ላይም የነበረውን ገደብ አንስቶታል፡፡ እንዲሁም ዝርዝር የሆነ የህብረቶችን ዓላማም አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህም ለጋራ ግቦች ስኬታማነት አባሎቻቸውን ማስተባበር እንዲሁም መደገፍ የሃሳብ፣ የመረጃ እና የልምድ ልውውጦችን ማካሄድ፣ የአባላትን አቅም መገንባትና ሀብት የማሰባሰብ ጥረታቸውን መደገፍ፣ የአባላትን የስነ-ምግባር እና የሙያ ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችሉ ስራዎችን ማከናወን፣ የአባላት የጋራ ድምፅ በመሆን የአባላትን የጋራ መብትና ጥቅም ማስከበር እና ለአባሎቻቸው የሥራ ሁኔታ እንዲፈጠር መሚገት፣ አባሎቻቸው በተሠማሩበት የስራ ዘርፍ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የፖሊሲ ሙግት እና የድጋፍ ስራዎችን ማከናወን ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ህብረት አባል ድርጅቱ ከሚሰራበት የስራ ዘርፍ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ስራዎችን በመስራት ከአባል ድርጅት ጋር ውድድር ውስጥ መግባት አይችልም፡፡ ሆኖም በአዋጁ አንቀፅ 56(3) መሠረት ህብረቶች ሀብት በማሰባሰብ በአባሎቻቸው አማካኝነት የፕሮጀክት ስራዎችን ማከናወን ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ፕሮጀክቶችን በቀጥታ ማከናወን አይችሉም፡፡

የዘርፍ ህብረቶች አባሎቻቸው በተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የፖሊሲ ሙግት እና ድጋፍ ሥራዎችን ማከናወን ይችላሉ በሚለው የአዋጁ ድንጋጌ ላይ የተለየ ትኩረት ልንሰጠው ይገባል። በዚህ ረገድ ህብረቶች በአባሎቻቸው የፖሊሲ ተሳትፎ ልምድ እና የምርምር አቅም ላይ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። የህብረቶች ለመንግስት ማማከርና የሙግት ሥራ የመስራት ሚና እንደጤና፣ ትምህርት፣ ሰብዓዊ መብቶች፣ የሴቶች መብት፣ የአርብቶ አደር ጉዳዮች እና በመሳሰሉት የተወሰኑ ዘርፎች ላይ ስለሆነ ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል።

በመጨረሻም አዲሱ አዋጅ በግልፅ ህብረቶችም የራሳቸውን ህብረት መፍጠር እንደሚችሉ ይደነግጋል። ይህም የህብረቶች ህብረት ይባላል። በተለያዩ ደረጃዎችም ሊመሠረት ይችላል። ማለትም በጂዎግራፊካል (በክልል ወይም በፌደራል) ወይም ከዓላማ አንፃር መመስረት ይችላል። የድርጅቶች ምክር ቤት የህብረቶች ህብረት የበላይ አካል ነው። ይህም ምክር ቤት የድርጅቶችን የራስ አስተዳደር ለማጎልበት እና ዘርፉን ከመንግስት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የሚያደርጉትን ግንኙነቶች እንዲወክል በአዋጁ ተቋቁሟል።

## ያስታውሱ፡-

ሁሉም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ከበጎ አድራጎት ኮሚቴ በስተቀር ለመንቀሳቀስ መመዝገብ ይኖርባቸዋል።

# ምዕራፍ 6
# በአዲሱ አዋጅ የተካተቱ የስራ ጉዳዮች

# ምዕራፍ 6

# በአዲሱ አዋጅ የተካተቱ የስራ ጉዳዮች

## 6.1 የስራ ነፃነት

ይህ በአዲሱ አዋጅ ከተጠበቁት መሠረታዊ መብቶች አንዱ ነው። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችም ዓላማቸውን ለመምረጥ እና ለመንቀሳቀስ ነፃ ናቸው። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችም በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ እንዲሁም ከማህበረሰቡ ፖሊሲ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ሁሉ ላይ መስራት ይችላሉ። ከዚህ አንፃር የአዋጁ አንቀፅ 62 ማንኛውም ድርጅት የተቋቋመበትን ህጋዊ ዓላማ ለማሳካት በየትኛውም ህጋዊ ስራ ላይ የመሰማራት ሙሉ መብት እንዳለው ይደነግጋል። በዚህም አዋጁ የስራ ነፃነትን በሙሉ ሁኔታ የሚሰጥ እና ከኢፌዴሪ ህገ-መንግስት እና ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አህጉራዊ፣ ክፍለ-አህጉራዊ፣ ሀገራዊ ወይም ክልላዊ ዓላማ ይዘው ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ። በአዋጁ አንቀፅ 62(4) በግልፅ እንደተቀመጠውም ድርጅቶች የሚያከናውኗቸው ስራዎች ጋር ግንኙነት ወይም ተያያዥነት ያላቸውን በስራ ላይ ያሉ ህጎች፣ፖሊሲዎች፣ አሰራሮች እንዲለወጡ፣ እንዲሻሻሉ ወይም አዲስ ህጎችና ፖሊሲዎች እንዲወጡ ሃሳብ ማቅረብ ይችላሉ።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ስለመንግስት ህግ ወይም ፖሊሲዎች ትችትን እንዲያቀርቡ አሊያም ሰብዓዊ መብቶችና መሠረታዊ ነፃነቶች እንዲጠበቁ እና እንዲጎለብቱ መሞገት እና መወትወት እንዲችሉ ተፈቅዷል።

ለዚህ ጠቅላላ ድንጋጌ ጥቂት ገደቦች አሉት። ከነዚህም የመጀመሪያው ህጋዊ ያልሆኑ ተግባራት ላይ መሳተፍ አይችሉም። እነሱም በድርጅቶች መተዳደሪያ ደንብ ከተጠቀሱት ዓላማዎች ውጪ፣ በሌሎች ህጎች የተከለከሉ ወይም እንደወንጀል ከሚቆጠር እንቅስቃሴዎች መቆጠብ ይኖርባቸዋል። ሁለተኛ፤ የውጭ ድርጅቶች ወይም በውጭ ዜጎች ኢትዮጵያ ውስጥ የተመሠረቱ ድርጅቶች በሌሎች ህጎች እስካልተፈቀደላቸው በቀር በመራጮች ትምህርት፣ በምርጫ መታዘብ እና ፖለቲካ ፓርቲዎችን መወትወት ላይ መሳተፍ አይችሉም። በሶስተኝነት፤ ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ ወይም ለሶስተኛ ወገን ጥቅም የሚሰሩ ድርጅቶች የሴቶችን፣ የህፃናትን፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የአዛውንቶች እና ሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት መስራት አለባቸው። በአራተኛ ደረጃ፤ ድርጅቶች እንቅስቃሴያቸው በሌሎች ህጎች ልዩ ፈቃድ መጠየቅ አለመጠየቁን ማረጋገጥ አለባቸው።

ያልተፈቀዱ ተግባራት፤ እባክዎን የሚከተሉት ተግባራት መከልከላቸውን ይገንዘቡ

- ህጋዊ ያልሆኑ ተግባራት፤
- የውጭ ድርጅቶች ያለፈቃድ የሚያደርጉት የመራጮች ትምህርት እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ውትወታ፤
- ተጋላጭ እና የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን አለማካተት፤
- በሌሎች ህጎች ልዩ ፈቃድ የሚጠይቁ ስራዎች ላይ መሠማራት፤

## 6.2 ሀብት፣ የማፈላለግ፣ የመቀበል እና የመጠቀም መብት

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ህልውናቸው እንዲቀጥል እና ዓላማቸውን ለማስፈፀም ሀብት ያስፈልጋቸዋል። ለዚህም ሀብት የማግኘት መብት ከመደራጀት መብት መሠረታውያን ውስጥ አንዱ ነው። ለዚህም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚከተሉትን መብቶች የሚያካትቱ መብቶች ሊኖራቸው ይገባል።

- የፋይናንስ ሀብት (ልገሳዎች፣ ዕርዳታዎች፣ በግል ድጋፍ የሚደረጉ ፈንዶች፣ የአባልነት ክፍያ፣ ከህዝብ መሰብሰብ፣የገቢ ማሰባሰቢያ እንቅስቃሴዎች)
- በአይነት የሚደረጉ ልገሳዎች ( ዕቃዎች፣ አገልግሎቶች እና የተለያዩ ምርቶች)
- ቁሶች (የቢሮ ዕቃዎች፣ የአይቲ ዕቃዎች፤)
- የሰው ሀብት (ሰራተኞች)
- አለም ዓቀፍ ድጋፎችን ማግኘት
- የተለያዩ ዕድሎች (ስልጠናዎች፣የሙግት ስብሰባዎች፣ የሽርክና ህንፃዎች)

በፓሪሱ የዕርዳታ ውጤታማነት ድንጋጌ (2005) እና በአክራ አጀንዳ ለተግባር (2008) መንግስታት እና ለጋሾች የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለልማት የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ ለማሳደግ የማስቻያ ሁኔታዎችን የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ እንዲፈጥሩ  ይደነግጋሉ። ዓለም ዓቀፉ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶችን አስገዳጅ የሆኑ ትርጓሜዎችን እንዲሰጥ ስልጣን የተሰጠው የተመድ ሰብዓዊ መብት ጉባዔ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ሀብት የማግኘት መብት የሚከላከሉ የተለያዩ ትርጓሜዎችን፣ ድንጋጌዎችን፣ ውሳኔዎችንና ሪፖርቶችን አስቀምጧል። በተመሳሳይ መልኩ የአፍሪካ የሰብዓዊች እና ህዝባዊ መብቶች ኮሚሽን የመሰብሰብ እና የመደራጀት መብቶች መመሪያዎች፤ መንግስታት ለትርፍ ላልሆኑ ዓላማዎች ተደራጅቶ ሀብትን የማሰባሰብ፣የመቀበል እና የመጠቀም መብትን እውቅና የሚሰጡ ህጎችን እንዲደነግጉ ጥሪ ያቀርባል።

ከዚህም ጋር ተያይዞ አዲሱ አዋጅ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከማንኛውም ህጋዊ ምንጭ ገቢ እንዲያገኙ እና እሱንም እንዲያስጠብቁ እውቅና ይሰጣል።  በአዋጁም አንቀፅ 61(4) እንደተጠቀሰው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት የመሆን፣ ንብረት የማስተዳደርና የማስተላለፍ መብት አላቸው እንዲሁም ዓላማቸውን ለማስፈፀም ከማንኛውም ህጋዊ ምንጭ ፈንድ የመቀበል እና የመጠቀም መብቶች አሏቸው። በተጨማሪም አዋጁ በማንኛውም ህጋዊ ንግድ እና ኢንቨስትመንት እንዲሁም በሌሎች ገቢ ማሰባሰቢያ ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ ይፈቅዳል።

> **የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፤  የንግድ ድርጅቶች ውስጥ ሼር የመያዝ፣ ገቢ የማሰባሰብ እና ከማንኛውም ለጋሾች እንዲሁም ግለሰቦችና የግል ድርጅቶች ስጦታንና ልገሳን መጠየቅ ይችላሉ፡፡**

አዋጁ ሀብት የማግኘት መብትን ሲፈቅድ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተጠያቂነታቸውንም ለማረጋገጥ ጥንቃቄዎችን አስቀምጧል። ለዚህም አዋጁ ማንኛውም ከድርጅቱ ጋር ግንኙነት ላለው ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ግላዊ ጥቅም እንዳያቀርቡ ይከለክላል። በአዋጁ አንቀፅ 62(11) በመርህ ደረጃ እንደተቀመጠው ማንኛውም የድርጅት አባል፣ አመራርና ሰራተኞች ስራቸውን በሚያከናውኑባቸው ወቅት የድርጅቱን ጥቅም የማስቀደም እና ከእነርሱ ጥቅም ጋርም እንዳይጋጭ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው ይላል። አዋጁ በግልፅ እንዳስቀመጠው የድርጅቱ ገቢና ሀብት ለግለሰቦች እንደማይከፈል አስቀምጧል። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መተዳደሪያ ደንብ ውስጥም በአዋጁ አንቀፅ 60(1መ) መሠረት < < የድርጅቱ ገቢና ሀብት ለአባላት እንዲሁም ለሰራተኞች በህግ ከተፈቀደ የአገልግሎት ክፍያ በስተቀር ሊከፋፈል የማይችል መሆኑን > > መያዝ እንዳለበት ይደነግጋል። በተጨማሪም አዋጁ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ የድርጅቱ አባላትም ሆኑ ሰራተኞች አባል ወይም ሰራተኛ በመሆናቸው ብቻ በድርጅቱ ሐብት ላይ ምንም አይነት መብት እንደሌላቸው በግልፅ ማስቀመጥ እንዳለባቸው ይደነግጋል።

## 6.3 ውስጣዊ የፋይናንስ ቁጥጥር ስርዓት

ውስጣዊ የፋይናንስ ቁጥጥር ስርዓት መኖር የፈንድን አያያዝ በመቆጣጠር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሀብታቸውን ይጠብቃል። ይህም ለጋሾች እና ለሚመለከታቸው አካላት የድርጅቱ ሀብት በጥንቃቄ ለቆመለት ዓላማ መዋሉን በማረጋገጥ አንድነትንና ውጤታማነትን ያረጋግጣል።

- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለህብረቶች አባላት ካልሆነ በስተቀር ትርፍን ለአባላት ለማከፋፈል ዓላማ አይመሠረቱም።
- ከንግድ እና ኢንቨስትመንተ የሚሰበሰበው ትርፍ ለአባላት አይተላለፍም።
- ከገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች የተገኙ ገቢዎች እና ሀብቶች ለድርጅቱ ሠራኞች ጥቅም አይተላለፉም።
- ከንብረቶች ማስወገድ የሚተርፉ ዕቃዎች ለአባላት ጥቅም ወይም ከድርጅቱ ዓላማ ውጪ ላሉ ተግባራት አይውሉም
- ድርጅቱ በሚፈርስበት ጊዜ ንብረቱ ለሌላ ተመሳሳይ ድርጅት አሊያም ለመንግስት ይተላለፋል
- የጥቅም ግጭት እንዳይኖር ተገቢውን እርምጃ መወሰድ ይኖበታል

## 6.4 የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አመራር

አንድ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት የህብረተሰቡን ጥቅም ለማረጋገጥ ውስጣዊ የቁጥጥር ስርዓት ሲኖረው መልካም አስተዳደርን እየተገበረ ነው ማለት ነው። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅም የተወሰኑ አስገዳጅ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ድርጅቶች አወቃቀራቸውና አስተዳደራቸውን የመወሰን መብት ያስቀምጣል። ስለዚህ የሰቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የውስጥ አመራራቸውን፣አወቃቀራቸውን፣ መሪዎቻቸውን የሚመርጡበት ደንቦችን፣ውስጣዊ የተጠያቂነት ዘዴዎችን እንዲሁም ሌሎች ፍላጎታቸውን የሚወስኑ ውስጣዊ አመራሮችን ለመምረጥ ነፃ ናቸው። ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አከላት ውስጥ ምንጊዜም ጠቅላላ ጉባዔው የበላይ ውሳኔ ሰጪ አካል ሲሆን ውሳኔዎቹና አቅጣጫዎችም ከሌሎች የድርጅቱ አካላት የበለጠ ገዢ ነው። ለእያንዳንዱ ወሳኔዎች ጠቅላላ ጉባዔውን መጥራት ስለማይቻል ድርጅቱ ማዕከላዊ ቦርድ ወይም አስፈፃሚ ኮሚቴ አቋቁሞ የማህበሩን የዕለት ተዕለት ተግባራትን እንዲከታተል ማድረግ ይቻላል (አንቀፅ 19)። በሌላ በኩል ቦርድ መር ድርጅቶች (ከ5-13 የሚደርሱ የቦርድ አባላት ያሉት፣ ቦርዱ የድርጅቱ የበላይ ውሳኔ ሰጪ እና ዘላቂ አስተዳዳሪ የሆነ (አንቀፅ 20)) በአንቀፅ 65 የተጠቀሱትን መስፈርቶች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አመራሮቻቸውን መምረጥ ይችላሉ።

> **በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ዘርፍ መልካም አስተዳደር << ግልፅ የሆነ የውሳኔ መስጠት ሂደት ማለትም ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት አመራር ውጤታማ እና ተጠያቂነት በተሞላበት መንገድ ሀብትን ሲመራ እና በጋራ ዕሴቶች መሰረት ስልጣንን ሲጠቀም ነው>>።**

ሆኖም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መስራቾች ወይም አባላት ትኩረት ሊሰጧቸው የሚገባ የተወሰኑ ገደቦች ወይም መርሆች አሉ። እነርሱም፡-

- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት አባልነት በበጎ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እና ማንኛውም በድርጅቱ የተጠቀሱትን የአባልነት መስፈርቶች ያሟላ ግለሰብ አባል የመሆን መብት አለው
- ውሳኔ በመስጠት ሂደት ውስጥ ሁሉም አባል እኩል ድምፅ አለው
- የድርጅቶች አመሰራረት እና ውስጣዊ አስተዳደር በዴሞክራሲ መርሆች፣ ከአድሎ የፀዱ ነፃ እና ገለልተኛ መሆን አለባቸው
- የድርጅቱ የቦርድ አባልም ሆነ የአስፈፃሚ ኮሚቴ አባል በተመሳሳይ ጊዜ የድርጅቱ ኦፊሰር ወይም ሰራተኛ ሆኖ ሊቀጠር አይችልም

## 6.5 ሪፖርት እና ቁጥጥር

### 6.5.1 የሪፖርት አይነቶች እና የሚቀርብበት ጊዜ

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለኤጀንሲው እና ለማህበረሰቡ የገንዘብ እንቅስቃሴያቸውን እና የስራ ክንውናቸውን ሪፖርት እንዲያደርጉ መጠየቅ አግባብ ነው። የድርጅቶቹን ግልፅነት እና ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የገንዘብ እንቅስቃሴ በሚመለከት ለተገቢው የመንግስት አካል፣ ለለጋሾች እና ለተጠቃሚዎች ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊጠየቁ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪም በኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ የሚንቀሳቀሱትን ድርጅቶች የታክስ ክፍያቸውን እንዲመዘግቡ መጠየቅ አግባብ ነው፤ ይህ ሲሆንም በሌላ የታክስ ከፋዮች ላይ የሚፈፀመው ህግ በድርጅቶቹም ላይ ተፈፃሚ ይሆናል። ለአነስተኛ እና ትልቅ ድርጅቶች የሚጠየቀው የሪፖርት ደረጃ አንድ ላይሆን ይችላል። በቂ ሃብት ያላቸው ትልቅ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሪፖርት በሚያደርጉበት ወቅት ሪፖርቱን የሚመለከቱ አጠቃላይ መስፈርቶች መሟላት ሲኖርባቸው አነስተኛ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከተወሰኑ መስፈርቶች ነፃ ሊደረጉ ይችላሉ።

አሁን ያለው የህግ ስርአት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የራሳቸውን ተጠያቂነት እና ግልፅነት እንዲያሰፍሩ የሚያበረታታ ነው። በአዋጁ አንቀፅ 71 መሠረት ሁሉም ድርጅቶች የገንዘብ እንቅስቃሴያቸውን የሚያሳይ ተቀባይነት ባለው የሒሳብ አሰራር የተዘጋጀ የሒሳብ መዝገብ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው። ነገር ግን አነስተኛ አመታዊ በጀት ያላቸው ድርጅቶች፤ አመታዊ በጀታቸው ከሁለት መቶ ሺ ብር የማይበልጥ ሲሆን፤ በራሳቸው በድርጅቶቹ የተዘጋጀ የሒሳብ መግለጫ ማስገባት ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪ ሕጉ የድርጅቱን ሃላፊዎች ቢያንስ የአምስት አመት የሒሳብ ቅጅ እንዲያስቀምጡ ያስገድዳል። በገንዘብ እንቅስቃሴ ሪፖርት ወይም በለጋሾች አልያም በመንግስት አካል ጥያቄ መሠረት ኤጀንሲው ድርጅቱን ተጨማሪ ነገሮችን ሊያስቀርበው ወይም በውጪ ኦዲት እንዲመረመር ሊያደርገው ይችላል።

## 6.5.2 ሪፖርት

ሕጉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት እዲያቀርቡ ይጠይቃል (አንቀፅ 73)። ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች እና ለማህበረሰቡ ክፍት መሆን አለበት። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት አመታዊ ሪፖርቱን የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ ሦስት ወራት ውስጥ ሳያቀርብ ሲቀር ኤጀንሲው የድርጅቱ አስተዳደራዊም ሆነ የመደበኛ ፍ/ቤት ይግባኝ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊው ማስታወቅያ በመስጠት እንዲፈርስ ሊወስን ይችላል። ኤጀንሲው ድርጅቱ በሰላሳ ቀናት ውስጥ መጥቶ እንዲያሳውቅ በጋዜጣ ሊጠራው ይችላል። ሆኖም ድርጅቱ በተሠጠው ጊዜ ካልቀረበ ኤጀንሲው ድርጅቱ እንዲፈርስ እና ከመዝገብ ላይ እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል። ይሄም እየሰሩ ያልሆኑ ድርጅቶችን ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ዝርዝር ለመሰረዝ ይጠቅማል።

**ኤጀንሲው በቂ ምክንያት ካለው፤ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱ አስፈላጊውን ማስጠንቀቅያ በመስጠት በስራ ሰዓታት የድርጅቱን ደብተር፣ የሒሳብ መዝገብ፣ ሰነዶችና የስራ ክንውን የመመርመር መብት አለው:: ይሄን መሰል ምርመራ በሚያደርግበት ጊዜ እጀንሲው የድርጅቱን የየዕለት ስራዎች በማይጎዳ መልኩ ማድረግ አለበት::**

## 6.6 እርምጃዎች

ከኤጀንሲው ስልጣናት መካከል አንዱ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ስራዎች በሕግ አግባብ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ነው። ኤጀንሲው ከሕዝብ፣ ከለጋሽ አካላት ወይም ከመንግስት ተቋማት ጥቆማዎች ወይም በራሱ በኤጀንሲው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱን ሪፖርት ምርመራ መሠረት፤ በሲቪል ማህበራት ድርጅቶቹ ላይ ምርመራ ሊጀምር ይችላል። ኤጀንሲውም የምርመራ ውጤቱን ተከትሎ የተለያዩ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል፤ እርምጃዎቹም ምክረ ሃሳቦችን የማቅረብ፣ ድርጅቱን የማገድ ወይም የማፍረስ ውሳኔ ሊሆን ይችላል። በጠቅላላው ሕጉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ሃላፊነት እና ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የተለያዩ መሣሪያዎችን ያስቀምጣል፤ እነዚህም፥-

- ለውጥን የማሳወቅ ግዴታ፤
- የምዝገባ የምስክር ወረቀትን በይፋ የማስቀመጥ ግዴታ፤
- ሲጠየቅ ሕልውናን የማረጋገጥ ግዴታ፤
- የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ፤
- አመታዊ የሒሳብ መግለጫን የማስገባት ግዴታ፤
- አመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርቱን ለኤጀንሲው የማቅረብ ግዴታ፤
- አመታዊ ሪፖርት ለሕዝብ ክፍት የማድረግ ግዴታ፤
- የባንክ ሒሳብ የመክፈት ግዴታ እና የባንክ ሒሳብ ወይም ፊርማዎች ለውጥ የማሳወቅ ግዴታ፤
- ማንኛውም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት የባንክ ሂሳብ ለመክፈት በቅድሚያ ከኤጀንሲው ፍቃድ ማግኘት አለበት።

ከአጀንሲው የቁጥጥር ሃላፊነት ትይዩ በሆነ መልኩ ሕጉ የሲቪል ማህበር ድርጅቶችን የመሰማት እና ወደ መደበኛ ፍ/ቤት የማምራት መብታቸው ያረጋግጣል (አንቀፅ 77፣ 78 እና 79)።

## 6.7 መዋሃድ፣ መከፈል እና መለወጥ

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በተለያዩ ምክንያቶች እርስ በእርስ ለመዋሃድ ወይም ለመከፈል አልያም ወደሌላ አደረጃጀት ለመለወጥ ሊወስኑ ይችላሉ። መዋሃድ ሁለት ወይም ከዛም በላይ የሆኑ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መቀላቀል ማለት ሲሆን፤ የድርጅቶቹ ሃብት እና እዳቸው አዲስ በውህደት ወደተፈጠረው ድርጅት ይተላለፋል ማለት ነው። በሌላ አገላለፅ፤ በውህደት ወቅት ቀድሞ ከነበሩት ሁለት የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የአንዱ ማንነት ወደ ሌላኛው ቀድሞ ወደ ነበረው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ይዋሃዳል ወይም ቀድሞ የነበረው አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዲስ የሲቪል ማህበር ድርጅት ይተላለፋል፤ ይህም የሚሆነው የቀደመ ሀብት እና እዳቸውን ወደ አዲሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት በማስተላለፍ ይሆናል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ወደ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወደ ሆኑ እራሳቸውን የቻሉና ሕጋዊ ሠውነት ወዳላቸው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሊከፈል ይችላል፤ አዲሱ ድርጅትም የቀድሞውን ድርጅት ስራዎች ሊያከናውን ይችላል። የተከፈሉት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከቀደመው ድርጅት የተለየ ስራ የመስራት ብቻ ሳይሆን፤ የተለየ አደረጃጀትም ሊይዙ ይችላሉ። ለምሳሌ በአባላት ላይ የተመሠረተ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ለሁለት ተከፍሎ፤ አንዱ አባላትን መሠረት ያደረገ ሲሆን ሌላኛው የቦርድ መር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ሊሆን ይችላል። በተመሳሳይ የቦርድ መር ሆኖ የተመሠረተ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት አባልነትን መሠረት ወዳደረገ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት መቀየር ይችላል። በዚህ ሁሉ መዘንጋት የሌለበት፤ የቀድሞው ድርጅት መብትና ግዴታዎች ወደተከፈለው ወይም ወደ ሌላ አደረጃጀት ወደ ተቀየረው ድርጅት የሚተላለፍ መሆኑን ነው።

አዲሱ ህግ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን መዋሃድ፣ መከፈል እና ወደ ሌላ የሲቨል ማህበረሰብ አደረጃጀት መቀየርን ፈቅዶዋል። ይሄን መሠሉም ውሳኔ በሲቪል ማህበራት ድርጅቶቹ ከፍተኛ የአመራሮች፤ ያለማንም ጣልቃ ገብነት እና ተፅእኖ መደረግ አለበት።

**ምንም እንኳን በህጉ ላይ በግልፅ ባይቀመጥም፤ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የንግድ ድርጅት ለመመስረት መዋሃድ፣ መከፈል ወይም መቀየር አይችሉም፡፡**

## 6.8 አስተዳደራዊ እርምጃዎች

የአዋጁ ክፍል አምስት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ለማስፈን የሚያስችሉ መንገዶችን ያመላክታል። መንግስት ሕዝብን ከመጭበርበር እና ከመብት ጥሰት ለመጠበቅ የተለያዩ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት። በቀጣይ እንደምንመለከተው ህጉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በተናጠል ወይም በጋራ የራሳቸውን ተጠያቂነት እና ግልፅነት እንዲያሰፍኑ ያበረታታል። ኤጀንሲው የሲቪል ማህበራት አዋጁን ወይም የራሱን ህጎች/ደንቦች በሚጥሱ የሲቨል ማህበረሰብ ድርጅቶች ላይ አስተደደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል። የህግ ጥሰቶቹ የሚከተሉትን ሊይዝ ይችላል፤ አመታዊ ሪፖርት አለማቅረብ ወይም ሪፖርቱን ማዘግየት፣ ሃሰተኛ ሪፖርት ማቅረብ፣ በህጉ ላይ ያሳውቁ ተብለው የተጠቀሱ ለውጦችን አለማሳወቅ፣ ሕገ ወጥ ከሆነ ምንጮች ገንዘብ መቀበል ወይም ህገወጥ ስራ ላይ መሳተፍ። ስለሆነም እንደ ድርጅቱ ጥፋት ባህሪና ክብደት ኤጀንሲው ወይም ቦርዱ አልያም ፍ/ቤት የተለያዩ አይነት እርምጃዎችን ሊወስዱ። በሕጉ ላይ የተቀመጡት እርምጃዎች ሂደታዊ ሲሆኑ.፤ ይግባኝ ሊጠየቅባቸውም የሚችሉ ናቸው። ይህ ክፍል በህጉ ላይ የተዘረዘሩ ዋና ዋና እርምጃዎችን እና የመቆጣጠርያ መንገዶች የሚዳሰሱበት ይሆናል።

## 6.8.1 ማስጠንቀቂያ

ሕጉ ሁለት አይነት ማስጠንቀቅያዎችን ያመላክታል፤ እነዚህም፡- ምክረ ሃሳብ እና ጥብቅ ማስጠንቀቅያዎች ናቸው። የድርጅቱ ድርጊት ቀላል የሚባል ጥፋት ከሆነ እና ጥፋቱም በማስተካከያ እርምጃ ይስተካከላል ብሎ ካመነ ኤጀንሲው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱ ሊወስድ ስለሚገባው የማስተካከያ እርምጃዎች ላይ ምክረ ሃሳቡን ይሰጣል። ኤጀንሲውም ምክረ ሃሳቡን ባቀረበበት ፅሁፍ የተፈፀመውን የህግ ጥሰት፣ ሊደረግ ስለሚገባው ማስተከከያ እና ማስተካከያውም በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መስተከካል እንዳለበት ማስቀመጥ ይኖርበታል (አንቀፅ 78(1)) ። ድርጅቱም የተሠጠውን ምክረ ሃሳብ ያልተገበረ እንደሆነ ወይም የፈፀመው ጥፋት ከባድ የሚባል ከሆነ፤ ኤጀንሲው ለድርጅቱ ጥብቅ ማስጠንቀቅያ ይሰጣል (አንቀፅ 78(2))። ባጠቃላይ ኤጀንሲው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱ ህግን ወይም የራሱን መተዳደርያ ደንብ እየጣሰ መሆኑን ከደመደመ፤ ማስተካከያዎችን ሊያዝ ከዛም አልፎ ጥብቅ የፅሁፍ ማስጠንቀቅያ ሊሰጥ ይችላል።

## 6.8.2 እገዳ

አዲሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ህግ ድርጅቶች ሊታገዱ፣ ሊፈርሱ እና ከመዝገብ ሊሰረዙ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ጨምሮ በማን ሊፈርሱ እንደሚችሉ ያስቀምጣል። በህጉ ከተጠቀሱ አስተዳደራዊ እርምጃዎችም አንዱ የኤጀንሲው ዳይሬክተር ድርጅቱ ከባድ የህግ ጥሰት መፈፀሙን ሲያረጋግጥና በዚህም ምክንያት የድርጅቱ እንቅስቃሴ ማገድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የእግድ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን ነው። ይህም ዳይሬክተሩ ጥፋቶች እንዳይባባሱ በጊዜያዊነት ሊወስድ የሚችለው እርምጃ ነው። በእገዳው ወቅት ድርጅቱ ሁለት አማራጮች አሉት፤ የመጀመሪያ አማራጭ በኤጀንሲው የሚሰጡትን የማስተካከያ ምክረ ሃሳቦች ወስዶ መተግበር አልያም ይግባኙን ለኤጀንሲው ቦርዱ ማቅረብ ነው። ነገርግን ከሁለት አንዱን አለማድረግ ድርጅቱን ወደ ሚቀጥለው ከፍ ያለ እርምጃ ሊዳርገው ይችላል፤ ይህም መፍረስ ይሆናል። ድርጅቱ ይግባኙን ለቦርዱ አቅርቦ፤ በቦርዱም ውሳኔ ቅር ከተሰኘ ቀጣይ ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ/ቤት ማቅረብ ይችላል።

## 6.8.3 መፍረስ እና ከመዝገብ መሠረዝ

የሰቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈርሱ ወይም ስራቸውን ሊያቆሙ ይችለሉ። ከነዚህም ውስጥ፤ የገንዘብ እጥረት፣ የተቋቋሙበትን አላማ ማሳካት፣ ድርጅቱ የተቋቋመበት ጊዜ ማብቃቱ፣ በአስተዳደራዊ እርምጃ ወይም የፍ/ቤት ትዕዛዝ ሊሆን ይችላል። አዲሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሕግ ድርጅት የሚፈርስበትን እና ከመዝገብ የሚሠረዝበትን መነሻ ምክንያቶች ያስቀምጣል። በሕጉ ላይ እንደተቀመጠው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት በራሱ ፍቃድ ወይም ያለ ፈቃዱ ሊፈርስ ይችላል። በሕጉ ላይ በግልጽ እንደተመላከተው ከፍተኛ የድርጅቱ አካላት (የጠቅላላ ጉባዔው ወይም ቦርዱ) የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱ እንዲፈርስ መወሰን ይችላሉ። የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብም ድርጅቱ የሚፈርስበትን መነሻ ምክንያቶች እና ስነስርአት ሊያስቀምጥ ይችላል። ስለሆነም ጠቅላላ ጉባዔው፣ ቦርዱ ወይም ሌላ ስልጣን የተሰጠው አካል ድርጅቱ እንዲፈርስ ሊወስን ይችላል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት በኤጀንሲው ወይም በፍ/ቤት ውሳኔ ሊፈርስ ይችላል፤ ይህም የመጨረሻ የእርምጃ አማራጭ ሊወሰድ ይገባል። ድርጅቱ ኤጀንሲው ያቀረበውን የማስተካከያ ነጥቦች ለመውሰድ ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር (አንቀፅ 78(4)) ወይም ተጠርቶ መኖሩን ማረጋገጥ ሳይችል ሲቀር (አንቀፅ 70) የኤጀንሲው ቦርድ ድርጅቱ እንዲፈርስ ሊወስንበት ይችላል። በተጨማሪም "ድርጅቱ በከባድ የወንጀል ድርጊት ወይም በተደጋጋሚ በቀላል ወንጀል በመሳተፍ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ" የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱ እንፈርስ ሊወስን ይችላል። በአጠቃላይ የድርጅት ከራስ ፈቃድ ውጪ መፍረስ የመጨረሻ አማራጭ ሲሆን፤ ድርጅቱ ቸግሮቹን እንዲፈታ ጊዜ ከተሰጠው ወይም ከባድ እና ጉልህ የሕግ ጥሰት ከፈፀመ የሚመጣ እርምጃ ነው። ሕጉ የድርጅቶችን መብት ለማስጠበቅ ሁለት ማስጠበቂያዎችን የሰስቀመጠ ሲሆን እነዚህም የመሰማት እና ወደ መደበኛ ፍ/ቤት የማምራት መብት ናቸው።

## 6.9 የመሰማት መብት

የሕጉ አንቀፅ 79 የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ላይ ማንኛውም እርምጃ ከመወሰዱ በፊት የመሰሰማት መብታቸውን አረጋግጦዋል። ድርጅቱ ለተከሰሰበት ጉዳይ ላይ መከላከያውን እንዲቀርብ በቂ ጊዜ ሊሰጠው ይገባል። ድርጅቱም እራሱን መከላከል ይችል ዘንድ ባለስልጣኑ፤ ድርጅቱ ተላለፈ ስለተባለው ሕግ በቂና ግልጽ መረጃ ሊሰጠው ይገባል። ከሁሉም በላይ ኤጀንሲው ድርጅቱ ያቀረበውን የመከላከያ በማስረጃ በገለልተኝነት መመርመር አለበት።

## 6.10 የመፍረስ ውጤቶች

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት መፍረስ ሁለት ውጤት ይኖረዋል፤ ይሄም፡- የሒሳብ መጣራት እና ከመዝገብ መሠረዝ ነው። የሒሳብ መጣራት ማለት የፈረሰ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ሃብትን በማስተላለፍ እዳው የሚከፈልበት ሂደት ነው። ይህ ስነ ስርዓት የድርጅቱን አበዳሪዎች እና ባለ ድርሻ አካላት ለመጠበቅ የተቀረፀ ነው። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱ ስለ መፍረሱ (በፈቃደኝነት ወይም በፍ/ቤት በሚወሰን መፍረስ ጊዜ) ኤጀንሲው በአስራ አምስት (15) ቀን ውስጥ የድርጅቱን ሃብት ይዞ የሒሳብ አጣሪ እንዲሾም፤ መፍረሱን ማሳወቅ አለበት። ኤጀንሲው፤ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ሃብት አግባብነት ያለው መተላለፍ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ እና በሕግ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ የድርጅቱን ውሣኔ ከመተዳደሪያ ደንቡ አንፃር ሊገመግም ይችላል።

**ከህብረቶች በስተቀር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ወቅት ሃብታቸውን ለመስራቾች፣ ለቦርድ አባላት፣ ሠራተኞች፣ ለለጋሾች ወይም አባላት ማከፋፈል አይችሉም።**

የሒሳብ አጣሪው ከተሾመ በኋላ ቀድሞ የነበረው የድርጅት አስተዳዳሪ አካል ስልጣን አብቅቶ በሒሳብ አጣሪው የሚከወን ይሆናል። የሒሳብ አጣሪው የንብረት ዝርዝር፣ የገንዘብ መግለጫን ያዘጋጃል እንዲሁም በጋዜጣ ወይም በሌላ መንገድ አበዳሪዎችን ይጠራል። የድርጅቱን እዳዎች እና የማፍረስ ሂደትን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ወጪዎች ተጠናቀው ከተከፈለ በኋላ ሒሳብ አጣሪው የድርጅቱን ቀሪ ሃብት በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ወይም በሕግ መሠረት እንዲተላለፍ ያደርጋል።

ከመዝገብ መሠረዝ ሌላው የመፍረስ ውጤት ነው። የሒሳብ አጣሪው ስራውን ማጠናቀቁን ለኤጀንሲው ካሳወቀ በኋላ ኤጀንሲው ድርጅቱን ከመዝገብ ይሰርዛል።

## 6.11 ራስን የማስተዳደር ማዕቀፍ

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ግልፅነትን እና ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ያለመ ራስን የማስተዳደሪያ መለኪያ እንዲያዳብር ይበረታታሉ። አዲሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሕግም ድርጅቶች ከፍተኛ የስራ እና አቋም መመዘኛ እንዲያስቀምጡ ያበረታታል። ከዚህ አላማው አንፃር አዲሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሕግ ም/ቤት ያቋቋመ ሲሆን፤ ም/ቤቱም፡-

- ከኤጀንሲው፣ ከለጋሾችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር ዘርፉ ሊከተለው የሚገባውን የስነምግባር ደንብና ማስፈጸሚያ ስልት ያወጣል፣ አተገባበሩን በቅርበት ይከታተላል፤
- በድርጅቶች ምዝገባና አስተዳደር ላይ ለኤጀንሲውና ለቦርዱ ምክረ-ሃሳብ ያቀርባል፤
- ዘርፉን ይወክላል፣ ያስተባብራል፤
- የራሱን የውስጥ ደንብ ያዘጋጃል።

ሁሉም ምዝገባ ያከናወኑ ድርጅቶች በራሳቸው ተሳትፎ በሚመራው ም/ቤቱ አባል እንዲሆኑ ይጠበቃል። የም/ቤቱ መቋቋም ራስን የማስተዳደር ስርዓቱን ያጠናክረዋል።

ACLP

CIVIL SOCIETY
RESOURCE CENTER

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ

Ferderal Democratic Republic of Ethiopia
AGENCY FOR CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS